# ዓምደ ሃይማኖት

ከዚህ በፊት ስለመንፈስ ቅዱስ ማንነት ስንገልጽ በስነ ልሳን አመለካከት የቃሉን አገባብ የትመጣነቱን ለማስረዳት ሞክረናል። በዚህ እትም ለማሳየት የምንፈልገው ስለመንፈስ ቅዱስና ምሳሌዎቹ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ለመንፈስ ቅዱስ ብዙ ምሳሌዎች አሉት። በብሉያትም በሐዲሳትም በተለያዩ ነገሮች ተምሳሌ እናገኝዋለን። መንፈስ ቅዱስ በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርታችን እንዳየነው ወዳልነው ሐሳብ እንመለሳለን ለመኾኑ መንፈስ ቅዱስ በምን በምን ይመሰላል ምንም እንኳን ለመንፈስ ቅዱስ ከፍጡር ወገን እንደ መንፈስ ቅዱስነቱ ባሕርይና አካል ሊገልጸው የሚችል እሱን የሚመስል ምሳሌ ባይገኝለትም አባቶቻችን ሊቃውንት እንዳስረዱን በመጽሐፍ ቅዱሳችንም ተመዝግቦ እንደምናገኘው መንፈስ ቅዱስ በብዙ ነገሮች ይመሰላል። በፀሐይ ሙቀት፣ በእሳት ዋዕይ፣ በሰው ነፍስ እስትንፋስ፣ በባሕር በዚህ አገባበ ጽላሎት ምሳሌ ተብሎ ይፈታል እንጂ ድንኳን አይባልም። የትርጉም ስሕተት ነው ካለው በዚህ ምእራፍ በቁጥር ፬ በምሳሌያዊ አነጋገር ስለ ስለነፍጥረት የፈጣሪን ሀልውና አስረጅነት የተጠቀሰው ኃይለ ቃል በምሥጢራዊ ፍቹ የነቢያትና የሐዋርያት ትንቢትና ስብከት በዓለም ሁሉ መዳረሱን የሚገልጽ መኾኑን በማስተዋል እንመርምር «ድምጻቸው ወደ ምድር ሁሉ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ» (መዝ.፲፰:፬)

## መንፈስ ቅዱስና ምሳሌዎቹ

ከቅድስት ሥላሴ ሶስተኛው አካል ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሠረፀ በአካላዊ ግብሩ ሠራጺ ተብሎ የሚጠራ በዚህ ስም የሚታወቅ ነው። መንፈስ ቅዱስ ለአብና ለወልድ የባሕርይ እስትንፋሳቸው (የባሕርይ ሕይወታቸው) ነው። ከአብና ከወልድ ጋር በሕልውና ያለ የሚኖር እንደ አብ እንደወልድ ያለ አካል ያለው አካላዊ ባሕርያዊ እስትንፋስ ነው። መንፈስ ቅድስ አካል የለሽ ዝርው ኃይል አይደለም መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ሳይለይ የፍጥረት አስገኝ የሁሉ ፈጣሪ ነው። መንፈስ ቅዱስ በመለኮት በሕልውና በባሕርይ በአገዛዝ በፈቃድ ከወልድና ከአብ ጋር አንድ ነው። ልብነትን ከአብ ቃልነትን ከወልድ ነሥቶ በአብ ልብነት ያስባል፣ በወልድ ቃልነት ይናገራል። እስከዚህ ድረስ ስለ መንፈስ ቅዱስ አጠቃላይ ዕውቀት እንዲኖረን የተገለጸው በቂ ሆኖ ለወደፊት በዝርዝር በማስረጃ አስደግፈን እስክንመጣበት ይቆየን።

ከላይ እንዳመለከት ነው መንፈስ ቅዱስ በብዙ ነገሮች ይመሰላል ሑሰት፣ በነፋስ፣ በርግብ፣ በቅብዓ ዘይት፣ በወይንና በውኃ ይመሰላል። መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ ነገሮች እንዴት እንደሚመለስ አንድ በአንድ እንመልከት።

### ሀ. መንፈስ ቅዱስ በፀሐይ ሙቀት ስለመመሰሉ

ነቢዩ ዳዊት የስነ ፍጥረትን ነገር የነቢያትን ትንቢት የሐዋርያትን ስብከት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ በተናገረበት ድርሳነ መዝሙር የምሥጢረ ሥላሴን ነገር በፀሐይ መስሎ ተናግሮታል። ጠቅላላ ትርጓሜውን ለመረዳት የመዝሙረ ዳዊትን አንድ ምታ ይመለከቷል። የግዕዙ ዳዊት ንባቡ «ወውስተ ፀሐይ ሤመ ጽላሎቶ» ይላል (መዝ.፲፰:፭) ትርጉሙ በነጠላው ምሳሌውን በፀሐይ አኖረ ወይም ፀሐይን ምሳሌው አደረገ ማለት ነው። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙር ፲፰/፲፱ በቁጥር ፭ ላይ «በእነርሱም ውስጥ የፀሐይን ድንኳን አደረገ» ብሎ ይፈታዋል «ጽላሎት» ተብሎ በግዕዝ የተጠቀሰውን ድንኳን ብሎ ፈትቶታል። ተብሎ የተነገረው ስለ ነቢያት ትንቢት ስለ ሐዋርያት ስብከት በሁሉ ዘንድ መሰማቱን መታወቁን የሚገልጽ ትንቢታዊ ቃል ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ስለዚህ ነገር አረጋግጦ ጽፎልናል። ንባቡም ትርጓሜውም እነሆ ይመልከቱ «ወባሕቱ እብል ቦኑ ኢሰምዑ እስራኤል አኮኑ ይቤ መጽሐፍ ውስተኩሉ ምድር ወፅአ ነገሮሙ እስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ። ...ነገር ግን እስራኤል አልሰሙም እላለሁን እንደሰሙ ሲያጠይቅ መጽሐፍ እንዲህ ብሎ የለምን። የነቢያት ትንቢታቸው የሐዋርያት ትምህርታቸው ባራቱ ማዕዘን ተነገረ ነገራቸው ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ደረሰ ብሎ የለምን? (ሮሜ.፲+፲፰) እንግዲህ ማስረጃውን እንደተመለከት ነው። «ወውስተ ፀሐይ ሤመ ጽላሎቶ ምሳሌውን በፀሐይ አኖረ ወይም ፀሐይን ምሳሌው አደረገ» ተብሎ የተጠቀሰው ትንቢታዊ ቃል በቁሙ ግዕዛን (አእምሮ ዕውቀት) ስለሌላቸው የስነ ፍጥረት አካላት ለፀሐይ ለጨረቃና ለከዋክብት ለጠፈር ለዕለታት ብቻ የተነገረ





www.ethiopisnorthodox.org

አድርገን እንድናስብ ያደርገናል። በአንጻሩ ስናይ ትንቢታዊ ቃሉ ለነቢያትና ለሐዋርያትም የተነገረ ስለ ምሥጢረ ሥላሴም የሚያስረዳ መኾኑን ያስገነዝበናል።

መንፈስ ቅዱስ በፀሐይ ሙቀት ይመሰላል ወደ ተባለው ሐሳብ እንመለስ ነቢዩ «ምሳሌውን በፀሐይ አኖረ» ብሏል ምን ማለቱ ነው ብለን እንጠይቅ መልሱ ልዑል እግዚአብሔር የራሱን ምሳሌ በፀሐይ አኖረ ፀሐይን ምሳሌው አደረገ ማለት ነው። እግዚአብሔር ሥላሴ መሆኑን በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርታችን ዐውቀናል። ፀሐይ ለእግዚአብሔር ምሳሌነቱ እንዴት ነው? ብለን እንመርምር። ለፀሐይ ሶስት ነገር አላት ክበብ፣ ብርሃን፣ ሙቀት አላት። በፀሐይ ክበብ (አካል) እግዚአብሔር አብ ይመስላል በብርሃኗ እግዚአብሔር ወልድ ይመሰላል በሙቀቷ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመስላል። ከፀሐይ ክበብ (አካል) ብርሃን ይወለዳል። ሙቀት ይሰርጻል (ይወጣል) ብርሃን የሚገኘው ሙቀትም የሚወጣው ከፀሐይ አካል ነው የፀሐይ አካል የብርሃንና የሙቀት መገኛ መሠረት ነው።

አካለ ፀሐይ (የፀሐይ ክበብ) ብርሃንና ሙቀትን ይልካል ብርሃንና ሙቀትም ከፀሐይ አካል ሳይለዩ ይወርዳሉ ጨለማንና ቅዝቃዜን በማራቅ የፍጥረትን ሕይወት ይጠብቃሉ። ብርሃንና ሙቀት ወደ ዓለም የሚላኩት ከፀሐይ አካል በመገኘት ቢኾንም በዓለም ሳሉ ከፀሐይ አካል ሳይለዩ በፀሐይ ክበብ ህልውሆነው ይኖራሉ። ስለ ፀሐይ ምንነት በገለጽነው ተምሳሌት አኳያ የሥላሴን ነገር እንይ። ከፀሐይ ክበብ ብርሃን እንደሚወለድ ከአብ አካልና ባሕርይ በብርሃን የተመሰለው ወልድ ይወለዳል። ከፀሐይ አካል ሙቀት እንደሚሰርፅ (እንደሚወጣ) ከአብ አካልና ባሕርይ ጰራቅሊጦስ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ይሠርጻል (ይገኛል) ብርሃን የሚገኘው ሙቀትም የሚወ ጣው ከፀሐይ አካል እንደኾነ እንደዚሁም ብርሃን የተባለው ወልድ በሙቀት የተመሰለው መንፈስ ቅዱስ ከእውነተኛው ፀሐይ ከአብ አካልና ባሕርይ ይወጣሉ (ይገኛሉ) የወልድ ከአብ መገኘት በልደት ሲኾን የመንፈስ ቅዱስ መውጣት ደግሞ በሥርፀት ነው። የፀሐይ አካል የብርሃንና የሙቀት መገኛ መሠረት ነው ባልነውም ምሳሌ በፀሐይ አካል የመሰልነው አብ ለወልድና ለመንፈስ ቅድስ መገኛ መሠረት ነው። ለወልድ መወለድ ለመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ መሠረቱ መገኛው አብ ብቻ ነው። ለዚህም ማስረጃው ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅድስ ዲዮናስዮስ፣ ቅድስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ ቄርሎስ በድርሳኖቻቸው «የሥላሴ መሠረት አንድ ነው እሱም አብ» ብለው አስተምረውናል።

የፀሐይ አካል ብርሃንና ሙቀትን እንደሚልክ አብም ወልድናመንፈስ ቅዱስን ይልካል። ብርሃንና ሙቀትም ከፀሐይ አካል ሳይለዩ እንደሚወርዱ ወልድና መንፈስ ቅዱስም ከአብ ሳይለዩ ይወርዳሉ የዚህም ትርጓሜው አብ በተለየ አካሉ ፈናዊ (ላኪ) የሁሉ መገኛ ነው። ወልድም በተለየ አካሉ ተፈናዊ (ተላኪ) ነው መንፈስ ቅዱስም በተለየ አካሉ ተፈናዊ (ተላኪ) ነው ማለት ነው።

ብርሃንና ሙቀት ከክበበ ፀሐይ ሳይለዩ ጨለማንና ቅዝቃዜን በማራቅ የፍጥረት ሕይወት ጠብቀው ሕይወት እንደሚኾኑ ወልድና መንፈስ ቅዱስም ከአብ አንድነት ሳይለዩ በኃጢአት ጨለማ የጠቆረውን በጽድቅ ብርሃን ያበራሉ በዓለም ፍቅር በክህደት በመናፍቅነት በአምልኮተ ጣዖት የቀዘቀዘውን ሕይወት በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ በጣዕመ መንግሥተ ሰማያት በጸጋ አሙቀው ሕይወት ይሆኑታል። ይጠብቁታል። ብርሃንና ሙቀት ወደ ዓለም የሚላኩት ከፀሐይ አካል በመገኘት ቢኾንም በዓለም ሳሉ ከፀሐይ አካል ሳይለዩ በፀሐይ ክበብ ህልው ሆነው እንደሚኖሩ ወልድና መንፈስ ቅዱስም ወደ ዓለም ተላኩ ስንል ከአብ አካል የተገኙ መኾናቸውን በማወቅ ቢኾንም በዓለም ሳሉ ከዓለም ውጭም መኖራቸውን ከማጤን ጋር ከአብ ሳይለዩ በአብ ሕልው ሆነው ይኖራሉ ማለታችን ነው።

ስለዚህም ከ፰ቱ ሐዲሳት መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ሥላሴ በፀሐይ መመሰላቸው ተጽፏል ለሐዋርያት ጌታችን የነገራቸው ቀሌምንጦስ ጽፎልናል። ቃሉም እንደዚህ የሚል ነው «አቡየ ፀሐይ ወአነ ብርሃኑ ወመንፈስ ቅዱስ ዋዕዩ... አባቴ ፀሐይ ነው ማለት ክበብ እኔ ብርሃኑ ነኝ መንፈስ ቅዱስም ሙቀቱ ነው። አባ ሕርያቆስም በቅዳሴ ማርያም አብ ፀሐይ ወልድ ፀሐይ መንፈስ ቅዱስ ፀሐይ አሐዱ ውእቱ ፀሐየ ጽድቅ ዘላዕለኩሉ» ብለዋል ትርጉሙም «አብ ፀሐይ ይባላል። ወልድም ፀሐይ ይባላል። መንፈስ ቅዱስም ፀሐይ ይባላል ለሁሉ የሚያበራ አንድ ባሕርያዊ ፀሐይ ይባላሉ» ማለት ነው ፀሐይ አንድ ሲሆን ፫ትነት አለው ይኸውም አካሉ ብርሃኑ ሙቀቱ ነው ፀሐይ ወጣ ሲባል አካሉ ይታወቃል የፀሐይ ብርሃን ታየ ሲባል ብርሃኑ ይታወቃል ፀሐይ ሞቀ ሲባል ሙቀቱ ይታወቃል። በአካሉ አብ ብርሃኑ ወልድ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመስላሉ።

መንፈስ ቅዱስ በፀሐይ ሙቀት ተመስሎ በጥላቻና በኃጢአት የቀዘቀዘውን ሕይወታችንን በሚለግሰን የጸጋ ፍቅሩና ጽድቁ የመንፈሳዊነት ሙቀትን እየሰጠ በመንፈሳዊ ሕይወት ሰውነታችን እንዲነድ እንዲመስጥ ያደርጋል። ይኸንን በማስመልከት አባቶቻችን መንፈስ ቅዱስ ሰማዕታትን አናዶ ወደ ደም ጻድቃንን አናዶ ወደ ገዳም ይወስዳቸዋል ብለው ስለ ሙቀተ መንፈስ ቅዱስ ይገልጻሉ። ስለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ክታቡ «በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ» ያለው (ሮሜ ፰+፲፬) የክርስቲያን ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ ሙቀት የጋለ መኾን ይኖርበታል። መንፈስ



www.ethiopisnorthodox.org

ቅዱስ የተለየው ሕይወት ሙቀት በተለየው በረዶና ቀዝቃዛ ፈሳሽ ይመስላል። በረዶው ወይም ቀዝቃዛው ፈሳሽ ሙቀት ስለተለየው አካባቢውን እንደሚያቀዘቅዝ መንፈስ ቅዱስ የተለየውም ክርስቲያን ለመንፈሳዊ ነገር ለቀና ሃይማኖትና ለበጎ ምግባር ስሜት የለሽ ይኾናል፤ ለኃጢአት ሥራና ለአምልኮተ ጣዖት ለኑፋቄ ተግባር ግን ይነቃቃል፤ በቀዝቃዛ ስሜቱም በአካባቢው ያሉትን ክርስቲያኖች እያቀዘቀዘ ደንታ ቢሶች ዓለማውያን ያደርጋቸዋል። ከዚህ ተሻልኩ የሚለው ደግሞ ለብ ያለ መሐል ሠፋሪ ክርስቲያን አለ ይኸም ፍቅሩ ሙሉ ስላልኾነ በአደገኛ ሕይወት ውስጥ የሚገኝ ነው።

ተወዳጅነት ያለው ሕይወት ሙቀት የተዋሐደው ፈሳሽ ሙሉ በሙሉ ትኩስ የሚፈጅ ያልቀዘቀው ለብ ያላለው ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ በፍጹም እምነታችንና ታዛዥነታችን ካደረብን ሕይወታችን በጸጋው የሞቀ የጋለ ይሆናል። ለአካባቢውም መንፈሳዊ ሙቀትን ያተርፋል።

ስለዚህ በፀሐይ ሙቀት የተመሰለው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንዳይለየን ሰውነታችንን በኃጢአት ለብ አናድርገው ልቡናችንንም በጥርጥርና በጣዖት አምልኮት አናቀዝቅዘው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ክርስቶስ ተገልጾለት በራእዩ ያሠፈረውን ምክር እንስማ «በረድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ በረድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር እንዲሁ ለብ ስላልህ ከአፌ ልተፋህ ነው።» ይላል። (ራእይ ፫፥፲፭–፲፮)

በረድ መኾን ማለት መንፈሳዊነትን ማጣት ዓለማዊ መኾን ማለት ነው። ዓለማዊ ነኝ የሚል ሰው ከጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሙቀት የተለየ መኾኑን ተገንዝቦ ንስሐ ለመግባት ዕድል ይኖረዋል። ኃጢአተኝነቱን ስለሚያውቅ መንፈሳዊነኝ ብሎ አይመጻደቅምና፤ ትኩስ የኾነውም እውነተኛ መንፈሳዊነት ያለው ክርስቲያን ነው በንስሐ ተመልሶ በሥጋው ደሙ ተጠብቆ ምግባር ትሩፋት በመሥራት በተዋሕዶ ሃይማኖት ጸንቶ ስለሚኖር የመንፈስ ቅዱስ የጸጋው ሙቀት ስለማይለየው በመንፈስ የሚቃጠል ይሆናል። ለምሳሌ የእስክንድርያው ሰው አጵሎስ በመንፈስ ይቃጠል እንደነበር ወንጌላዊ ሉቃስ በግብረ ሐዋርያት የጻፈውን እንመልከት «የሐዋ.ሥራ ፲፰፥፳፬–፳፰) ለብ ያለው ግን እንደ ይሁዳ አስቆሮቱ ክርስቶስን ከመሸጥ ተዋሕዶ ሃይማኖቱን ለገንዘብ ሲል ከመለወጥ ይደርሳል ወይም እንደ ዴማስ አስመሳይ ክርስቲያን ይሆናል። ለሆዱ ሲል ከመስቀል ሕይወት ይኮበልላል ከወንጌል ዓላማ ይወጣል እንዲህ ከመኾን መጠበቅ የሚቻለው የመንፈስ ቅዱስ ሙቀትን እንዳይለይን ሲኾን ነው። (ማቴ.፳፮፥፲፭–፲፮፡ ፪ኛጢሞ.፬፥፱)

ለ. <u>መንፈስ ቅዱስ በእሳት ዋዕይ ይመሰላል</u>: ዋዕይ ሙቀት ማለት ነው መንፈስ ቅዱስ በዋዕየ እሳት ወይም በእሳት ሙቀት ይመሰላል። ከላይ በፀሐይ ምሳሌ እንዳየነው ሥላሴ በእሳት ይመሰላሉ እሳት አንድ ሲሆን ሦስትነት አለው ይኸውም አካሉ ብርሃኑ ሙቀቱ ነው። አካሉ እሳት ነደደ ሲባል ይታወቃል። ብርሃኑ እሳት በራ ሲባል ይታወቃል። ሙቀቱ እሳት ሞቀ ሲባል ይታወቃል። በአካሉ አብ፤ በብርሃኑ ወልድ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ እሳት አንድ ሲሆን ሦስትነት እንዳለው ሦስትነት ሳለው አንድ እንደሆነ ሥላሴም በአካል ሦስት በባሕርይ በሕልውና አንድ ናቸው። ስለዚህ ነገር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ለሐዋርያት እንዲህ ሲል ነግሯቸዋል «አቡየ እሳት ወአነ ብርሃን ወመንፈስ ቅዱስ ዋዕዩ» «አባቴ እሳት ነው እኔ ብርሃን ነኝ መንፈስ ቅዱስም ዋዕዩ ነው» ብሏል (ቀሌምንጦስ)

አባሕርያቆስም በቅዳሴ ማርያም «አብ እሳት ወልድ እሳት ወመንፈስ ቅዱስ እሳት አሐዱ ውእቱ እሳተ ሕይወት ዘእምአርያም» «አብ እሳት ይባላል፤ ወልድ እሳት ይባላል፤ መንፈስ ቅዱስ እሳት ይባላል በልዕልና ያለ ሕይወትነት ያለው አንድ እሳት ይባላሉ።» ብለዋል። በእሳቱ አካል አብ በብርሃኑ ወልድ በሙቀቱ መንፈስ ቅዱስ ይመስላል የእሳት ዋዕይ (ሙቀቱ) ከብርሃኑና ከእሳቱ አካል አይለይም። መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ አይለይም በአብና በወልድ ህልው ነው የእሳት ዋዕይ (ሙቀት) ከእሳቱና ከብርሃኑ ሳይለይ በሥራው ማለትም በመፋጀቱ ተለይቶ ይታወቃል መንፈስ ቅዱስም በባሕርይ በሕልውና ከአብና ከወልድ ሳይለይ በተለየ አካሉ በሠራጺነት ከአብና ከወልድ ተለይቶ ይታወቃል ሠራጺ መንፈስ ቅዱስ ይባላል እንጂ

## ስጡኝ መነጽሬን

የዓይኔ ብርሃን ራቆ ማየት ስላልቻለ፤
ጨለማ ሁኖበት ሲደናበር ዋለ።
የገዛ አካሌ እግሬ ከእግሬ ጋር፤
ጎዳናውን ስቶ ሲደነባበር።
ሾፌር እንደሌለው ካሚዮን መኪና፤
የሚመራው ጠፍቶ በር ይጋጭና።
እንዳልሆን ሁኖ ተንከባሉ ገደል፤
ያለአንዳች እርባና ጠፍኖ እንደሚውል፤
እንደዚሁ ሆኖብኝ የሕይወቴ ነገር፤
የተፈጥሮ ዓይኔ ቢከለል ቢታወር።
እግሬ ከእግሬ ጋር ከአካሌ ተጋጭቶ፤
ጠልፎ እንዳይጥለኝ መንገዱን አስቶ።
መነጽሬን ስጡኝ የዓይኖቼን ብርሃን፤
አጉልቶ እንዲያሳየኝ መስመር ጎዳናውን።
ስጡኝ መነጽሬን የዓይኖቼን ረዳት፤
ከሕይወት ጎዳና ወጥቼ እንዳልስት፤
የዓይኖቼ መነጽር ይምጣ በቅጽበት።
መነጽር ያልኳችሁ ሰው ሠራሽ መስሏችሁ፤
ከየመሸጫው ሱቅ ከኪዮስክ ገዝታችሁ፤
ገዙትን መስታወት ብትሰጡኝ ፈጥናችሁ።
የጥያቄዬን ውል ሐሳቡን ሳታውቁ፤
እታምጡ መነጽር ካሁኑ ተጠንቀቁ።
መነጽር ያልኳችሁ ሁሉን የሚያሳየኝ፤
ወንጌል ነው ምሥጢሩ ያዕቆብ የነገረኝ።
የያዕቆብ መስታወት የቃሉን ትምህርት፤
ስጡኝ መነጽሬን ራሴን ልይበት።



www.ethiopisnorthodox.org

ወላዲ አብ ተወላዲ ወልድ አይባልም።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን በእሳት ይመስለዋል የነቢያት አለቃ ሙሴ እግዚአብሔርን በእሳት መስሎ ይነገረናል። በኦሪት ዘዳግም ምዕ. ፬፥፲፩ ላይ «እግዚአብሔር በኮሬብ በእሳት ውስጥ ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ መልክ ከቶ አላያችሁምና እጅግ ተጠንቀቁ እንዳትረክሱ» ካለ በኋላ በኮሬብ እሳት ውስጥ የተገለጸውን አምላክ በቁጥር ፳፬ «አምላክህ እግዚአብሔር የሚበላ እሳት ቀናተኛም አምላክ ነውና» ብሎ እግዚአብሔርን በእሳት ይመስለዋል። ስለዚህ ነው በሊቃውንት ትርጓሜ አብ እሳት ነው፣ ወልድ እሳት ነው፣ መንፈስ ቅዱስም እሳት ነው የተባለው እሳት ሁለት ጠባይ አለው ያቃጥላል ሕይወትም ይሆናል እግዚአብሔርም እንደ እሳት ፈታሒነትም መሐሪነትም ስላለው በከፋዎች ላይ ፈርዶ ይቀጣቸዋል። ለደጋጎች ፈረዶ በምሕረቱ ይታደጋቸዋል፣ ያድናቸዋል። አባ ሕርያቆስም ስለዚህ ነበር እሳት ማኅያዊ ለርቱዓነ ልብ ለእለ ይገብሩ ፈቃዶ እሳት በላዒ ለዓማፅያን ለእለ ይክሕዱ ስሙ ያሉት (ቅዳ.ማር. ፩፥፯) ትርጉሙም «ፈቃዱን ለሚፈጽሙ የሚያድን እሳት ነው። ስመ አምላክነቱን ለሚክዱ ሰዎች የሚያቃጥል እሳት ነው» ማለት ነው። በቅዱስ ወንጌልም ተጽፎ እንደምናገኘው መጥምቁ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት በዮርዳኖስ እያጠመቀ ወደ እርሱ እየተናዘዙ ለሚመጡት እንዲህ ይላቸው ነበር። «ውእቱሰ ያጠምቀክሙ በመንፈስ ቅዱስ ወበእሳት። በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል።» (ማቴ. ፫፥፲፩) ክርስቶስ ሲመጣ በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ያመኑበትን የሚያጠምቅ እንቢተኞችን ግን በገሃነም እሳት የሚቀጣቸው አምላክ መኾኑን ሲገልጽላቸው የተናገረው የምስክርነት ቃል ነበር ከዚህ አነጋገር የምንወስደው ቁም ነገር አለ። መንፈስ ቅዱስ በእሳት ተመስሎ በአምሳለ እሳት ክርስቶስን ለሚከተሉ አማንያን የሚሰጥ መኾኑን ነው። የቅዱስ ዮሐንስ ትንቢት ጠብ አላለም በጊዜው በበዓለ ሃምሳ (በዘመን ጰራቅሊጦስ) ሐዋርያትና ሌሎችም በጠቅላላው መቶ ሃያው ቤተሰብ በተገኙበት መንፈስ ቅዱስ ጸጋውን በእሳት ላንቃ ከፋፍሎ ባደለ ጊዜ ተፈጽሞአል።

ቅዱስ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ምዕ. ፪፥፫ ላይ እንዲህ ሲል የትንቢቱን ፍጻሜ ይተርክልናል «ወአስተርአይዎሙ ልሳናተ እሳት ክፉላት ከመ እሳት ዘይትከፈል ወነበረ ዲበ ኵሉሙ ወተመልኡ ኵሉሙ መንፈስ ኃይል» ይላል። ትርጉሙም እነሆ «ላንቃ ላንቃ ያለው እሳት ሆኖ ታያቸው በአምሳለ እሳት ዘይትከፍል ይላል ላንቃ ላንቃ ባለው እሳት አምሳል ታያቸው ከመ እሳት ዘይትከፈል ይላል ላንቃ ላንቃ እንዳለው እሳት ሆኖ ታያቸው በሁሉም አደረባቸው ኃይል የሚሆናቸው ሀብትን ሀብት የሚሆናቸው ዕውቀትን ገንዘብ አደረጉ» ማለት ነው። ሀብት ያለው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋው ነው። ጸጋውም መንፈሳዊ ጥበበን ሰማያዊ ዕውቀትን የወንጌልን ምሥጢር ወንጌልን ለማስተማር የሚችሉበትን መንፈሳዊ ኃይልንና በዓለም ያሉትን ልሳናት (ቋንቋዎች) ሳይማሩ ማወቅን ሁሉ የሚያጠቃልል የመንፈስ ቅዱስ ሀብት ለምዕመናንና ሐዋርያት የተሰጠ ስጦታ ማለት ነው።

ስለዚህ ነገር ከደቂቃ ነቢያት አንዱ የሆነው ነቢዩ ኢዩኤል በትንቢቱ ገልጾዋል (ኢዩ.፪፥፳፰—፴፪)

«ወይከውን እምድኅረ ዝ መዋዕል ይቤ እግዚአብሔር እስውጥ እምነ መንፈስየ ዲበ ኵሉ ዘሥጋ» (የሐዋ. ሥራ ፪፥፲፯) «አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም በሥጋዊ በደማዊ ሰው ሁሉ የባሕርይ ሕይወቴ መንፈስ ቅዱስን አሳድርበታለሁ» «ወይትነበዩ ደቂቅክሙ ወአዋልዲክሙ ወወራዙቲክሙ ወሊቃውንቲክሙ ሕልመ የሐልሙ» «ወንዶች ልጆቻችሁ ሐዋርያት ሴቶች ልጆቻችሁ ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት እንስት ጎበዞቻችሁ ሰብአ አርድእት ትንቢት ይናገራሉ። ራእይ ያያሉ ሽማግሌዎቻችሁ ጴጥሮስ በኢዮጴ ሰገነት፣ ዮሐንስ በፍጥም ደሴት ራእይ ያያሉ።»

«ወላዕለ አግብረትየ ወአዕማትየ እከው እምነ መንፈስየ ወይእተ አሚረ ይትኔበዩ» (ቁ.፲፰) «በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ። ማለትም በቆርኔሊዎስ ቤተሰብ የባሕርይ ሕይወቴ መንፈስ ቅዱስን አሳድርባችኃለሁ ያን ጊዜ ሁሉም በሰባ ሁለት ቋንቋ ይናገራሉ። ከቁጥር ፲፱—፳፩» «ወእሁብ ትእምርተ በሰማይ በላዕሉ ወመንክረ በምድር በታሕቱ ደመ ወእሳተ ወጢሰ ፀሐይኒ ይጸልም ወወረኅኒ ደመ ይከውን ዘእንበለ ትብጻሕ ዕለተ እግዚአብሔር ዐባይ ወግርምት ወኵሉ ዘጸውዐ ስመ እግዚአብሔር ይድኅን»

ትርጉሙም እነሆ «በሰማይ ምልክት አሳያለሁ በምድርም ምልክት አሳያለሁ በሰማይ ላለው «ወእሳተ» ብሎ አመጣ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ እሳት ይሰጣል ደመ ብሎ ምድር ላለው አመጣ ደመወልድ እግዚአብሔር ይፈሳል «ወጢስ» ማለት ጢስ (ጭጋግ) ይሆናል ማለትም የመንፈስ ቅዱስ ሀብቱ የማይቆጠር የማይሰፈር ነው ብሎ ስለ ሀብቱ ብዛት «ወጢስ» ይለዋል ሰማይ ላለው አመጣ ፀሐይ ይጨልማል ጨረቃም ደም ይሆናል ብሎ ቀጥሎም «ወኵሉ ዘጸውዐ» ብሎ ዕለተ እግዚአብሔር ዕለተ ትንሣኤ ጌታ የተነሣበት ሰንበተ ክርስቲያን እሑዱ ሳትደርስ ስመ እግዚአብሔርን የጠራ ሁሉ ይድናል በቀኙ የተሰቀለው ወንበዴ ትንሣኤ ሳይደርስ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ ብሎ ድኗልና ከዚያን ጊዜ እንሥቶ እስከ ዕለተ ምጽአት ኹንደ ፈያታዊ ዘየማን ስሙን የሚጠሩ ሁሉ መዳናቸውን መናገሩ ነው።»

ወደዚህ ሐተታ የገባነው አለ ምክንያት አይደለም በነቢዩ ኢዩኤል



www.ethiopisnorthodox.org

እሳት ተብሎ የተጠቀሰው ትንቢት በዘመነ ሐዋርያት «በአምሳለ እሳት ወይም በእሳት ላንቃ ተመስሎ መንፈስ ቅዱስ ጸጋውን ማደሉን ለማስረዳት ትንቢትንና ፍጻሜውን አርእስትና ጎዳጉን ብሉይንና ሐዲስን በማስማማት ለማገናዘብ እንዲረዳን ብለን ነው። በጥንቃቄ ከተመለከትነው ምሥጢሩ ግልጽ እንደሚሆንልን አንጠራጠርም።

አሁን ወደ ተነሣንበት ርእስ ተመልሰን መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል ለምን እንደተመሰለ እንመልከት መንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰሉን በመጽሐፍ ቅዱስና በሉቃውንት ትርጉም ስላረጋገጥን እንዴት ይመስላል ማለት አይቻለንም አይሆንም መንፈስ ቅዱስ በእሳት የተመሰለበትን ምክንያት መምህራን ቤተክርስቲያን ያተቱልንን ሐተታ ትርጓሜያቸውን በማየት ማጥናቱ ይጠቅመናል። «ውእቱስ ያጠምቀክሙ በመንፈስ ቅዱስ ወደእሳት» (ማቴ.፫፥፲፩) «እሱ ግን በጅ ብትሉ በመንፈስ ቅዱስ በጅ ባትሉ በገሃነም እሳት ያጠምቃችኋል። አንድም በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ያጠምቃችኋል» ትርጓሜው የወንጌሉ ከዚህ ላይ የገለጽነው ነው። ወደ ሐተታው ሳንገባ መንፈስ ቅዱስ ለምን በእሳት ምሳሌ እንደተሰየመ እንረዳለን ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት መንፈስ ቅዱስን በእሳት ይመስለዋል ያለንብትን ምክንያት እንመርምር መንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰሉ ስለ ብዙ ምክንያት ነው። እሳት የሌለበት ቦታ አይገኝም በሁሉ ቦታ ይገኛል። በእንጨቱም በብረቱም በድንጊያውም ጽንፍ እስጽንፍ ስለሚገኝ ምሉዕ ነው። በሁሉ ቦታ የሚገኝ ነው። መንፈስ ቅዱስም እንደእሳት ምሉዕነት የማይገኝበት ሥፍራ የለም መንፈስ ቅዱስ ምንም በእሳት ቢመሰል እንደ እሳት በጊዜና በቦታ አይወሰንም። እሳት ፍጡር ስለኾነ ጉድለት አለበት እንደ መንፈስ ቅዱስ በሰማይና በምድር ከዚያም ውጭ መገኘት አይቻለውም የተፈጠረበት ጊዜና የሚያልፍበት ሰዓት አለው። በመንፈስ ቅዱስ ግን ይኸ ሁሉ የለበትም በሰማይና በምድር ከዚያም በላይና በታች እሱ ባወቀው በምልዓት ከአብና ከወልድ ጋር ጊዜ ና ቦታ ሳይወስነው ለዘላለም በምልዓት ያለና የሚኖር ምሉዕ በኩለሄ እምኔ ፐሬዘንት አምላክ ነው።

እሳት በሁሉ ቦታ በደንጊያውም በእንጨቱም በብረቱም በምልዓት ቢኖርም እሳትነቱ የሚገለጸው መኖሩ የሚታወቀው ቡላድ የመቱ እንደኾነ ነው። እሳት ቡላድ ካልመቱ ማለትም ካልጫሩት እንጨት ከእንጨት ካልሰበቁት ደንጊያን ከደንጊያ ብረትን ከብረት ካላፋጩት ክርቢትን ከቃፎው ጋር ካልጫሩትና ካላቀጣጠሉት የእሳት ህላዌ (አኗኗር) አይገለጽም አይታወቅም። መንፈስ ቅዱስም እንደ እሳት በቤተክርስቲያን አድሮ ሳለ ጥንትም በነቢያት ኋላም በሐዋርያት በረድኤትና በጸጋ አድሮ እያለ ቋንቋ ሲያናግር ምሥጢር ሲያስተረጉም

## መጽሔት አእምሮ

ጊዜ ወርቅ ነው በስንፍና በእንቅልፍ ሊያልፍ አይገባውም ጊዜን በሥራ ማሳለፍ የሰው ልጅ ዓይነተኛ ጠባይ ሊሆን ይገባል። ሰው ሆይ! ራስህን በየቀኑ ጠይቅ። ጊዜዬን በስንፍና አሳለፍኩትን? ወይስ ያለፈው ጊዜ በቁም ነገር ዋለን? እያልክ ጠይቅ። በስንፍና ካሳለፍከው ከእንግዲህ ወዲህ ይህንን ዓይነት ፍሬቢስ ልማት ተው። ጊዜህን በቁም ነገር አሳልፍ እንዲህ ያደረግህ እንደሆነ የጊዜን ወርቅነት ትረዳለህ።

ልታጠና የሚገባህን ዕውቀት ለዛሬ አጥና። ለነገ እያልክ አትቅጠር። ዛሬ ያንተ ቀን ነው። ነገ የሌላ ሊሆን ይችላል። በጊዜህ ሥራበት እንጂ ስንፍና በሕይወትህ እንዲሰለጥን አታድርገው።

በየቀኑ ክርስቲያናዊ ሕይወትህ ሊጐለምስ ይገባዋል። እግዚአብሔር በዚች ዓለም የተከለህ ዛፍ መሆንህን አትርሳ። ስለዚህም መልካም ፍሬን ለማፍራት አትቦዝን። በየቀኑ ንቦች ከአበባ ላይ ይቀስማሉ። የዛሬውን ለነገ አያሳድሩትም። ዛሬ የቀሰሙትን ዛሬውኑ የማር እንጀራ በማድረግ ይጋግሩታል።

አንተ ታላቅ ፍጡር ሰው መሆንህን አትዘንጋ። ከንቦች ማነስ አይገባህም። ከስነፍጥረት ተግባር። ሁሉም በጊዜው ሥራውን ያጠናቅቃል። ከጊዜው ዝንፍ አይልም። አንተስ በጊዜህ ልትሠራ ሲገባህ ለነገ ለምን ታሳድራለህ? በየቀኑ ክርስቲያናዊ ሕይወትን አሳድግ። ከውስጥህ የምታርመው አረም ካለ ዛሬውኑ ይታረም። ዛሬውኑ ሊያብብ የሚገባ ተግባር ካለህ ያብብ። የምታፈራው ፍሬ ካለ ዛሬውኑ አፍራው እንጂ በቀጠሮ አታሳድረው። በጊዜው ያላፈራችውን በለስ አትምሰል። ባለማፍራቷ በመርገም ደርቃለች። አንተም እንደእርሷ አታድርግ። በጊዜህ መልካም ፍሬን አፍራ። (ማቴ.፳፩፥፲፰—፲፱) በዛሬው ቀን መጸለይ የሚገባህን ተግባር። ጊዜ እየሰጠህ ዘወትር በተሰጠህ አእምሮ ሕይወትህን ፈትሻት! በሰውነትህ ውስጥ የዉለማ ጠባይ እንዳይኖር አስተውል። በጊዜው ጊዜ ሳይበላ እንደተቀረው የሻገተ እንጀራ አትሁን። የቆየ ነገር ይሻግታልና! ሕይወትህ በኃጢአት በስንፍና አይሻግት። አእምሮው መጽሔትህ ነው። ሕሊናህ መስታወትህ ነው ማለት ነው። ራስን በራስ መዝኖ ጉድለትን ከማረም የበለጠ ምን ነገር አለ። ሰው በትድግሢያ ራሱን ግምት ይኖርበታል። ራሱን ያወቀ ሰው ከመጠን ወጥቶ በኩራት አይዝናናም። ስሕተቱን ሌሎች ከማረማቸው በፊት በአእምሮው መጽሔት አስተውሎ ለማስወገድ ይጥራል። በእውነት ራሳችንን ብንመረምር ልማት ብቻ ሳይሆን ጥፋትም ይገኝብናል። ቅንነት ብቻ ሳይሆን ጥመት! ደግነት ብቻ ሳይሆን ክፋት የመሳሰለው በውስጣችን ይኖራል። በአጭር ቃል ድካማችንን እናስተውላለን። የሰውነትን ወይም የልብስን ዕድፍ ቶሎ ቶሎ በጊዜው በውኃ ማስለቀቅ አስፈላጊነቱ እያጠያይቅም። የነፍሳችንን ጉድፍ በየቀኑ ካላስወገድነው የኃጢአት ጥቅትት በርክቶ የሕይወታችን ጠንቅ ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ በጊዜያችን እንጠቀምበት። ጊዜያችንን በዋዛ ፈዛዛ በከንቱ አናሳልፍ። ዕድሜያችንን ውጤታማ የሆነ ሥራ በማሳየት ብናሳልፈው ይሻላል። ወገኖቻችን በጊዜያችን ቁም ነገር እንሥራበት። ሰውነታችን መልካም ፍሬ ሳታፈራ የመቃብር ሲሳይ አትሁን። ከመቃብር ግዶ ጥያቄ እንዳለብን አንዘንጋ። በተሰጠን እድሜ ሰውነታችንን እየመረመርን በአእምሮ መጽሔታችን (በሕሊና መስታወታችን) ራሳችንን እንወቅ። ስሕተታችንን እያረምን በንስሐ ሕይወታችንን እናስተካክል። ወርቅ ጊዜያችንን በከንቱ አናባክን። ሕሊናችንም መስታወታችን ይሁን። በመልካም ሕሊና ለመመራት ቅዱሳት መጻሕፍትን መመልከት እናዘውትር። በሕይወታችን መልካም ፍሬን ለማፍራት እንድንችል ቅዱስ መጽሐፍ ነፍሳችንን የሚያጠግብ የሕይወት ወንዝ መሆኑን እንወቅ። (መዝ.፩፥፪—፫) መድኃኒዓለም ክርስቶስ በድንግል እናቱ ምልጃ በጊዜያችን ተጠቅመን የሕይወት ፍሬ ለማፍራት ያብቃን አሜን።

ወሰብሐት ለእግዚአብሔር

መለኮት

www.ethiopisnorthodox.org

ትንቢት ሲገልጽ ራእይ ተከሥቶ ሲያመጣ ገቢረ ተአምራት ሲያሠራ ካልኾነ ማዳኑ መኖሩ አይታወቅም፤ አይከሰትም፤ እሳት ሲጭሩት ከቡላዱ ሲወጣ በመጠን ነው ኋላ በእንጨት እያቀጣጠሉ ያስፋታል። የመንፈስ ቅዱስም ጸጋው ሀብቱ በጥምቀተ ክርስትና ሲሰጥ ሲታደል በመጠን ነው ኋላ መንፈስ ቅዱስ የሚወደውን ሥራ ምግባር ትሩፋት እየሠሩ በሥራ ያስፋታል። ጸጋው እየበዛ ከወጣትነት ወደ ማዕከላዊነት ከዚያም ወደ ፍጹምነት መድረስ ይቻላል። ስለዚህ ነበር ቅዱስ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ መታተማቸውን ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ ብሎ በእምነትና በጥምቀት መንፈስ ቅዱስ እንዳደረባቸው ካረጋገጠላቸው በኋላ በኃጢአት ምክንያት እንዳይለያቸው ሲያስጠነቅቅ «መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አስትክሩ ይህ ማባከን ነውና» ብሎ የመከራቸው (ኤፌ.፩+፲፫ እና ፭+፲፰)

የመንፈስ ቅዱስ ጸጋው በየጊዜው የሚጨመረው ምዕመናን በንስሐ ከኃጢአት እየራቁ የመንፈስ ፍሬ ይኸውም የንስሐ ፍሬ በማፍራት ክርስቲያናዊ ሕይወታቸውን በገድል በትሩፋት ሲያጎለምሱ ነው። (ማቴ.፫+፰፤ ገላ.፭+፳፪፤ ፩ኛ ተሰሎ.፭+፳፪፤ ኤፌ.፩+፰፤ የሐዋ.ሥራ ፲፪+፩—፫) እሳት ጣዕምን መዓዛን ያመጣል። ጥሬውን እህል ብንቆላው ሊጡን ብንጋግረው ሥጋውን ብንቀቅለው ብንጠብሰው በእሳት ምክንያት ይጥማል መዓዛውም ያማረ ነው። ምግቦች ለአፋችን የሚጥሙት ለአፍንጫችን ደስ የሚያሰኙት ጥሩ ጣዕም መዓዛ የሚኖራቸው እሳት ሲነካቸው ነው። መንፈስ ቅዱስም በምዕመናን አድሮ ጣዕመ ጸጋን መዓዛ ጸጋን እየሰጠ ደስ ያሰኛል። ሕይወታችንን በጸጋው ያጣፍጥልናል መዓዛ ገነትንት ጣዕመ መንግሥተ ሰማያትን ያመጣልናል። በዚህም ነፍሳችን መከራውን ሁሉ ሳትሰቀቅ የክርስቶስን መከራውን የምትዘከርበትን መስቀሉን ተሸክማ በደስታ ተውጣ ትገኛለች። (ማቴ. ፲፮+፳፬፤ የሐዋ.ሥራ ፭+፵—፵፪፤ ሮሜ.፭+፫—፭)

እሳት በመጠን ቢሞቁት ሕይወት ይሆናል ከመጠን ወጥቶ የሞቁት እንደሆነ ግን ያቃጥላል መንፈስ ቅዱስም በሚገባ በተጻፈው የመረመሩት እንደሆነ ሕይወት ይሆናል በማይገባ ከተጻፈው ወጥቶ የመረመሩት እንደሆነ ግን ይቀስፋልና «ስሙን ለሚክዱት አምላክነቱን ለሚጠራጠሩት እንደ እነ መቅዶንዮስ እንደ እነ ረስል የአርዮስ ተከታዮች ፍጡር ቢሉት እንደ ዝርው ኃይል ቢቆጥሩት ያለ ግብሩ ግብር ያለ ባሕርዩ ባሕርይ ሲሰጡት የሚበላ እሳት ነው። ይፈርዳል ይቀጣል ይቀስፋል ከኃጢአትም አያነጻቸውም ለዘላለም በንስሐ ካልተመለሱ በወዲሁም በወዲያኛውም እሱ ባወቀ ይፈርድባቸዋል።

ለሚያምኑት ግን ፈቃዱን ለሚፈጽሙት ጸጋውን ያድላቸዋል። ከኃጢአት ይጠብቃቸዋል። በእምነት በተስፋ በፍቅር በመልካም ሥራ ሁሉ ያጸናቸዋል። ዘላለማዊ ሕይወትን ያጎናጽፋቸዋል። ነቢያትን ሐዋርያት ጻድቃን ሰማዕታት በጸጋው እንዳጎለመሳቸው ከፍጹምነት እንዳደረሳቸው በእውነት በፍጹም ትሕትና የሚገዙለትን ንጹሐን ቅዱሳን ያደርጋቸዋል። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስ የሚያድን፤ ሕይወትን የሚያድል እሳት ይባላል (ማቴ.፲፪+፴፩—፴፪፤ የሐዋ.ሥራ ፭+፩—፲፩፤ ዕብ.፮+፫—፰)

እሳት ያቀረቡለትን ሁሉ ያቃጥላል ውኃን ቢጥዱበት ያፈላዋል ሥጋውን ይጠብሰዋል ጥሬውን ይቆላል ይቀቅላል ከሰሉን ፍጉን ቅጠሉን ጭራሮውን የመሰለውን ሁሉ ያነድዋል። መንፈስ ቅዱስም ሕዝብ አሕዛብ የጸለዩትን ጸሎት ያቀረቡትን መሥዋእት መባቸውን ምጽዋታቸውን ትሩፋታቸውን ይቀበላል። ሰውነታቸውን በጸጋው ያሞቀዋል በመንፈሳዊ ፍቅር ያቀጣጥለዋል። ፈቃደ ሥጋን ይጠብሰዋል እንደገለባ አመድ አድርጎ ያሩን ሁሉ የሰይጣንን ተንኮል ሁሉ ያርቃል ያጠፋል ወጣኒውን ምዕመን በአእምሮ ያበስለዋል ሥጋውን ነፍሱን ልቡናውን ይቀድሰዋል። የኃጢአትን ግብር ሁሉ አርቆ ንጽሕናን ቅድስናን ይሰጣል። (፩ኛ ተሰሎ. ፭+፳፫፤ ሮሜ.፰+፲፩፤ ቆሮ.፲፪+፲፩ና፲፫) እሳት ውሀ ገደል ካልከለከለው ሁሉን ማጥፋት ማቃጠል ይቻለዋል። የእሳት ኃይል ደንጊያውን እንደ ቅቤ ያቀልጠዋል ይኸውም በከርሰ ምድር ባለው እሳተ ገሞራ ይታወቃል ማዕድናት ብረታ ብረት ሁሉ የሚቀልጠው በእሳት ኃይል ነው። መንፈስ ቅዱስም ቸርነቱ ካልከለከለው ሁሉን ላጥፋ ቢል ይቻለዋል የሚሳነው አንዳች ነገር የለውም ሁሉን ማድረግ የሚቻለው ፈራጅ አምላክ ነውና ከሰዎች መካከል የመንፈስ ቅዱስን ከሃሊነት አምነው በትሕትና በእምነት ቢቀርቡት እሳት ደንጊያውን ብረቱን ማቅለጥ እንደ ተቻለው መንፈስ ቅዱስም በኃጢአት በሥጋ ፈቃድ የደነደኑን ልቡናቸውን በንስሐ ሊያቀልጥላቸው የሚቻለው ባለጸጋ ጸጋን የሚያድል ነው።

እሳት ዱር ይገልጻል እሳት የበላው መሬትም ለእህል ለተክል ይመቻል። መንፈስ ቅዱስም ምሥጢር ይገልጻል መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰውነትም ለገድል ለትሩፋት ይመቻል ከዛጎላቸው ሳይሳተፍ ሰባቱን መዓድናት እሳት ያደራቸዋል መዓድናት ሁሉ ጥራት የሚያገኙት በእሳት ተፈትነው። መንፈስ ቅዱስም እንደ እሳት ከግብራቸው (ከሥራቸው) ሳይሳተፍ ሁሉን ይነጻልና።

እሳት ካንዱ ፋና (መብራት) አምሳ ስልሳ ፋና ቢያበሩለት ከዚያም በላይ ሲያበሩ ቢውሉ ቢያድሩ ተከፍሎ የለበትም አይቀነስም አይጎድልም። መንፈስ ቅዱስም ተከፍሎ ሳይኖርበት እስከ ምጽአት ድረስ ሲሰጥ ጸጋውን ሲያድል ይኖራልና ቢሰጥ የማያልቅበት በባሕርዩ ተከፍሎ ጉድለት የሌለበት ነውና።

መንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰሉና በአምሳለ እሳትም ለሐዋርያትና ለሌሎችም የተሰጣቸው እሳትን ለመዓት እንጂ ለምሕረት አልተፈጠረም ብለው እንዳይሳሳቱ ነው።



www.ethiopisnorthodox.org

ቀድሞ የሰዶም የገሞራን ሕዝብ ከእስራኤልም አንዱን ኅብር አጥፍቶበታል። በዚህ ምክንያት እሳት ለመቅጫ መቅሠፍት የተፈጠረ የሚመስላቸው ነበሩ። ይኖራሉም መንፈስ ቅዱስ ለመቶ ሃያው ቤተሰብ በበዓለ ሃምሳ ጸጋውን በአምሳለ እሳት በመስጠቱ ለምሕረት እንደተፈጠረ ሊረዱ ችለዋል። ይኸም እሳት ለመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ በመኾኑ ለመዓት ብቻ ሳይሆን ለደግ ነገርም የተሠራ መኾኑን አስገንዝቧቸዋል። (ዘፍጥ. ፲፱፥፳፬–፳፭ ይሁዳ ፩፥፯። ፪ኛ ነገሥ.፩:፩–፲፭) ሸክላ ሠሪ ሰርታ ሰርታ ስትጨርስ ነቅ ያገኘችበት እንደሆነ እንደገና መልሳ ከስክሳ በውሀ ለውሳ በእሳት ታድስዋለች። በሸክላ የተመሰሉ አዳምና ልጆቹም ኃጢአት በመሥራት ነቅ (ጉድለት) ተገኝቶባቸው የነፍስ ብልየት እርጅና ቢገጥማቸው በንስሐ ውሀና በጥምቀተ ክርስትና በመንፈስ ቅዱስ እሳትነት ታድሰው በክርስቶስ አምነው ስለተገኙ ታድሰዋል አዲስ ፍጥረት ሆነዋል። ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ የተገኘ ጸጋ ነው። ይኸንና ይኸንን በመሰለ ምክንያት መንፈስ ቅዱስ በእሳት ተመስሏል። በአምሳለ እሳት ለቅድስት ቤተክርስቲያን ተሰጥቷል። (፪ኛ ቆር.፭፥፲፯)

### ሐ. መንፈስ ቅዱስ በሰው ነፍስ በእስትንፋስነቷ ስለመመሰሉ

ሰው በአርአያ ሥላሴ መፈጠሩን ስለ ሰው ተፈጥሮ በሚናገረው ኦሪት ዘፍጥረት ተገልጿል። ሰውን በምሳሌያችን በመልካችን እንፍጠር ባለ ጊዜ ልዑል እግዚአብሔር ሥላሴነቱን ገልጿል ሰውም በአርአያ እግዚአብሔር መፈጠሩን አመልክቷል። ዝርዝር ሁኔታውን ለመገንዘብ በመጀመሪያው ዓመት የታተመችውን መለከት ቁጥር ፩ን መመልከት ይቻላል።

የሰው ነፍስ ሶስትነት አላት ልብ፣ ቃል፣ እስትንፋስ አላት። ይህ ሰው ለባዊ ነው ባልን ጊዜ ልቡን መናገራችን ነው። ነባቢ ነው ባልን ጊዜም ቃሉን መናገራችን ነው። ሕያው ነው ባልን ጊዜ እስትንፋሱን መናገራችን ነው። ለነፍሳችን ልብ ቃል፣ ሕይወት ቢኖራትም በዚህ ምክንያት የከዊን ሶስትነት አላት ይባላል። በአካል ግን አንድ ናት ሥላሴም በአካላት ሶስት በመለኮት ግን አንድ ይባላሉ በልብነቷ አብ፣ በቃልነቷ ወልድ በእስትንፋስነቷ መንፈስ ቅዱስ ይመስላል አረጋዊ መንፈሳዊ «ከመ ኢይትፈለጡ እምነፍስ ንባባ ወእስትንፍሳ ወሕይወተ ዚአሃ ከማሁ ኢይትፈለጡ እምአብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» ብሏል ትርጓሜውም ከነፍስ ንግግሯና ሕይወቷ የሚሆን እስትንፋሷ ከእርሷ እንደማይለዩ እንደዚሁ ወልድና መንፈስ ቅዱስም ከአብ አይለዩም» ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ በሰው ነፍስ በእስትንፋስነቷ መመሰሉ ይኸን በመሰለ አኳኋን ነው።

### መ. መንፈስ ቅዱስ በባሕር ሑሰት (በቀላይ እንቅስቃሴ ወይም ሁከት) ይመሰላል

ባሕር ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ለሶስትነታቸውም ለአንድነታቸውም በምሳሌነት ያገለግላል የባሕር ሶስትነቱ ስፋቱ፣ ርጥበቱ፣ ሑሰቱ (እንቅስቃሴው) ነው። በስፋቱ አብ፣ በርጥበቱ ወልድ፣ በሑሰቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ።

ነገር ግን አንድ ባሕር ይባላል እንጂ ሶስት እንደማይባል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስም አንድ አምላክ እንጂ ሶስት አማልክት አይባሉም አረጋዊ መንፈሳዊ ሥላሴን በባሕር መስሎ ሲያስረዳ ነጽርኬ ዘተብህለ በእንተ አበ ኩሉ ከመ መሰልዎ በዛቱ ባሕር እንተ ትትገሠሥ ወለወልድኑ ዘይሰገድ በኀበ ኩሉ ከመመሰልዎ በርጥበተ ማይ ወለመንፈስ ቅዱስኒ ዘይሴባሕ በኀቦ ኩሉ ከመመሰልዎ በሁከተ ማይ ብሏል «የሁሉን አባት በጸጋ ሁሉን የወለደውን አብን በዚች ቀላይ (ባሕር) እንደመሰሉት ተመልከት በሁሉ ዘንድ የሚሰገድለትን በሁሉ ዘንድ የሚመለከውን ወልድንም በውኃው ርጥበት መመሰላቸውን አስተውል በሁሉ ዘንድ በሰውም በመላእክትም የሚመሰገነውንም መንፈስ ቅዱስን በባሕሩ መናወጽ በንውድውድታው (በሁከቱ) እንደመሰሉንት እይ።» ማለት ነው።

ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በባሕር ሑሰት (እንቅስቃሴ) ተመስሏል የባሕሩ እንቅስቃሴ ንውድውድታው ከባሕሩ አካልና ርጥበት ሳይለይ እንደሚኖር ይታወቃል መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ ሳይለይ በአብና በወልድ ይኖራል ከአብና ከወልድ ጋር በባሕርይ በህልውና አንድ ነው የባሕሩ የውኃ አካል ርጥበትና ሑሰት በአንድነት ቀላይ (ባሕር) ተብሎ ይጠራል አንድ ባሕር ተብሎ ይታወቃል እንጂ ሶስት ባሕር አይባልም። በባሕሩ አካል የተመሰለው አብ፣ በርጥበቱ የተመሰለው ወልድ በሑሰት የተመሰለው መንፈስ ቅዱስ በአንድነት አንድ አምላክ አንድ እግዚአብሔር አንድ መለኮት ተብሎ ይጠራል። አንድ አምላክ ተብሎ ይታወቃል እንጂ ሶስት አማልክት ወይም ሶስት መለኮት ሶስት እግዚአብሔር አይባልም። መንፈስ ቅዱስ በሑሰት ተመስሏል ብለናል ሑሰት ከርጥበትና ከውኃው አካል አይለይም። ባልነው መሠረት መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም ከአብና ከወልድ ጋር በባሕርይ በህልውና አንድ ሆኖ ያለመለየት መኖሩን ተገንዝበን ስንገዛለትና ስናመሰግነው እንኑር። ✣

## እንንቃ

በ ዚህ ዓለም ሳለን ገና በሕይወት፤
ተ ንኩልን እንተው ሳይጠልፈን ያ ሞት።
ዋ ብለን ብናለቅስ ተይዘን በሥቃይ፤
ሕ ይወታችን አልፋ ሆነን የአፈር ሲሳይ።
ዶ ክተሩ ላይገኝ የሚያድን ዐዋቂ፤

ጽ ልመት ጣር ሳይወጣሽ ካሁኑ ተጠንቀቂ፤
ኑ እያልን እንምከራት ነፍሳችንን ንቂ።



www.ethiopisnorthodox.org

# ዓምደ ሃይማኖት

## መንፈስ ቅዱስና ምሳሌዎቹ

ካለፈው የቀጠለ

ሚሬክ ገብረክርስቶስ

በ፫ኛ ዓመት ቁጥር ፪ የመጋቢት ወር መለከት መጽሔታችን መንፈስ ቅዱስና ምሳሌዎቹ በሚለው ዐቢይ ርእስ ሥር መንፈስ ቅዱስ ሀ. በፀሐይ ሙቀት ስለመመሰሉ ለ. በእሳት ዋዕይ ስለመመሰሉ ሐ. መንፈስ ቅዱስ በሰው ነፍስ በእስትንፋስነቷ ስለመመሰሉና መ. መንፈስ ቅዱስ በባሕር ሑሰት (በቀላይ እንቅስቃሴ ወይም ሁከት) መመሰሉን መግለጻችን ይታወሳል። ምንም ምሳሌ ዋናውን ነገር አክሎና ሙሉ በሙሉ ተመሳስሎ መግለጽ ባይችልም በሌላ አባባል ምሳሌ ዘየሐፅፅ እንደሚባለው ቢሆንም በዚህ ጽሑፋችን መንፈስ ቅዱስ ከስነ ፍጥረት ክፍሎች በሌሎችም ነገሮች እንደሚመሰል የመጽሐፍ ቅዱስንና የሊቃውንትን ምስክርነት ዋቢ በመጥቀስ ለማስረዳት እንሞክራለንና አንባቢያን በጥንቃቄና በማስተዋል እንድትመለከቱት አደራ እንላለን።

### ሠ. መንፈስ ቅዱስ በነፋስ ስለመመሰሉ፤

ቅዱስ መጽሐፍ መንፈስ ቅዱስንና ሥራውን በነፋስ ይመስለዋል። ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ስለመወለድ ለኒቆዲሞስ መምህራችን ክርስቶስ ሲያስረዳው፤ ምሥጢሩ ቢጸነው፥ ትምህርቱ ባይገባው ከተፈጥሮ ዕለታዊ ክስተት ከነፋስ ጠባይና እንቅስቃሴ እንዲረዳ የመንፈስ ቅዱስን ነገር በነፋስ መስሎ ነግሮታል።

ቅድስ ዮሐንስ የመድሐኒታችንን ምሳሌያዊ ገለጻ እንዲህ ሲል ይገልጻዋል፤ «እስመ መንፈስ ኀበ ፈቀደ ይነፍሕ ወቃሎ ትሰምዕ፤ ወኢ.ተአምር እምኀበ ይመጽእ ወኀበሂ የሐውር ከማሁኬ ውእቱ ኩሉ ዘይትወለድ እመንፈስ ቅዱስ» (ዮሐ:፫+፰) ትርጉሙ በነጠላው እንደሚከተለው ይሆናል «ነፋስ በወደደው ይነፍሳል፥ ድምፁን ትሰማዋለህ የሚመጣበትን የሚሄድበትንም አታውቀውም። ከመንፈስ ቅዱስ የሚወለዱት ልደት እንዲህ ነው» ማለት ነው።

ነፋስ በወደደው ይነፍሳል ማለቱ ነፋስ ግዕዛን አለው ማለት አይደለም። ግዕዛን ያላቸው ከፍጡራን ሰውና መላእክት ናቸው። ግዕዛን ማለትም ነጻነት ወይም ነጻ ፈቃድ ማለት ነው። ወዶ ፈቅዶ የመረጡትን መሥራት ያልፈቀዱትን መተው በተፈጥሮ በተሰጣቸው ነፃነት ነጻ ፈቃድ ላላቸው ለሰውና ለመላእክት የሚነገር ነው የሁላችን መምህርና ፈጣሪ ክርስቶስ ነፋስን ለመንፈስ ቅዱስና ሥራው ምሳሌ አድርጎ በሰም አነጋገር በገለጠ ጊዜ ወርቁን ማለትም ዋናውን መሥጢር በማጉላት «ኀበ ፈቀደ ይነፍሕ= በወደደው ይነፍሳል» ብሏል። ምሥጢሩ ስለመንፈስ ቅዱስ የሚያሳይ ነው እንጂ በቁሙ ነፋስን አይመለከትም። የነፋስ መኖር የሚታወቀው ድምፁ ሲሰማ ነው፤ ነፋስ ሲነፍስ ባሕር ሲገስፅ፥ ዛፍ ሲያናውጽ ድምጹ ስለሚሰማ የነፋስ መኖር ይታወቃል። የሚመጣበትና የሚሄድበትን ግን አይታወቅም። በስነ ፍጥረት ትምህርት ለነፋስ በምሥራቅ ፮ በምዕራብ ፮ መሳከው (መስኮቶች) ማለትም መውጫ መግቢያ አቅጣጫዎች እንዳሉት ይነገራል፤ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በየትኛው ወጥቶ በየትኛው ተመልሶ እንደሚገባ እን[ደ]ሚያመራ አይታወቅም። ስለነፋስ ዙረትና አቅጣጫ በመጽሐፈ መክበብ ጥበበኛው ሰው ሰሎሞን ሲገልጽ «ነፋስ ወደ ደቡብ ይሄዳል ወደ ሰሜንም ይዞራል ዘወትር በዙረቱ ይዞራል ነፋስም በዙረቱ ደግሞ ይመለሳል» ብሏል። (መክ.፩+፮)

የነፋስ እንቅስቃሴና መኖሩ በተግባሩ እንጂ እንዲያው እንደማ ይታወቅ የመንፈስ ቅዱስ ሥራውና ህልውናውም በቅዱሳን በሚሠራው ሥራ ካልኾን አይታወቅም። የነፋስ አካሄድ አለመታወቅ ለመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሆኖ መቅረቡን እናስተውል። ምዕመናን ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ በጸጋ ረቂቅ ልደት ሲወለዱ በእምነት ካልኾነ በሥጋዊ ምርምር በደማዊ ዕውቀት ከቶ ሊረዱት የማይቻል በመኾኑ ነፋስ ዓይነተኛ ምሳሌ ሆኖ ቀርቧል። የቤተክርስቲያናችን ሊቃውንት ምሳሌውን ወደ ምሥጢር በመለወጥ በአንድምታ አካሄድ እንደሚከተለው ይተነትኑታል። ነፋስ ወደ ማንኛውም አቅጣጫ ሊነፍስ እንደሚችል መንፈስ ቅዱስም በረድኤቱ በወደደው ያድራል። ነፋስ ባሕር ሲገሥጽ ዛፍ ሲያናውጽ ድምጹን እንደሚያሰማ መንፈስ ቅዱስም ትንቢት ሲያናግር ሱባዔ ሲያስቆጥር፤ ቋንቋ ሲገልጽ ምሥጢር ሲያስተረጉም



www.ethiopisnorthodox.org

ይሰማል። ነፋስ የሚመጣበትና፣ የሚሄድበት እንደማይታወቅ የመንፈስ ቅዱስ ሀብቱ (ስጦታው) ከአንዱ ወደ ሌላው ሲተላለፍ ወይም ሲያድር አይታወቅም። ለምሳሌ ሀብተ ሙሴ በኢያሱ ሀብተ ኤልያስ በኤልሳዕ ሲያድር አልታወቀም ነበር። ዳግመኛም በዘመነ ሐዲስ በቅዱስ ጴጥሮስ ያደረው መንፈስ ቅዱስ በቆርኔሌዎስና በቤተሰቦቹ፣ በሐናንያ አድሮ የነበረው ሀብተ መንፈስ ቅዱስ በኋላ ጳውሎስ ተብሎ በተሰየመው በሳውል ሲያድርበት እንዳልታወቀ አይታወቅም ይኸም ማለት እንዴት እንደሚያድር ለይቶ ማወቅ አይቻልም ማለት ነው እንጂ አድሮማ ሥራ ሲያሠራቸው በተግባሩ ማወቅ ይቻላል። ነፋስ ሲነፍስ ከወዴት ተነሥቶ ወደየት እንደሚደርስ በውል መከታተል አይቻልም ከዚህ አለ ሲሉት ከወደዚያ ይገኛል ወዲያ አለ ሲሉት ከወዲሁ ይገኛል። መንፈስ ቅዱስም በሁሉም ቦታ ይገኛል። ከወዲያ አለ ከወዲህ የለም ከወዲያ ወዲህ ይመጣል ከወዲህ አለ ከወዲያ የለም ከወዲህ ወዲያ ይሄዳል አይባልም የመንፈስ ቅዱስ ህልውናው ሥራው የማይመረመር ምሥጢራዊ ነውና ስለኾነም መመርመር አይቻልም ከሰው ችሎታ በላይ ነው በአንክሮ በዕፁብ ሲደነቅ ይኖራል።

በሊቀ ነቢያት ሙሴ አድሮበት የነበረው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ማለትም ሀብተ መንፈስ ቅዱስ በኢያሱ ላይ ሲያድርበት በግልጽ አይታወቅም ነበር ሙሴ በአንብሮተ ዕድ ኢያሱን በባረከው ጊዜ ረቂቅ በሆነ ምሥጢር ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ለኢያሱ ሊሰጠው ችሏል። አንብሮተዕድ ማለትም እጆችን መጫን ማለት ነው እንደ ሙሴ ያለ ሰው መንፈስ ቅዱስ ያደረበት እንደ ኢያሱ ባለ ሰው ላይ እጆችን በራሱ ጭኖ ሲባርከው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታው ከባራኪው ወደ ተባራኪው ይተላለፋል። በሌላ አነጋገር መንፈስ ቅዱስ በረድኤት ስለሚኅበኘው ጸጋውንም ስለሚያሳድርበት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ይሆናል ማለት ነው። ለዚሁም ማስረጃው «ሙሴም እጆቹን ስለ ጫነበት የነዌ ልጅ ኢያሱ የጥበብን መንፈስ ተሞላ» ይላል (ዘዳግ.፴፬ ቁ.፱) መንፈስ ቅዱስ ያላደረበት ሰው በድፍረት ተነሣሥቶ በሐሰት ሳያድርበት አድሮብኛል ብሎ እጆቹን ልጫንባችሁ ቢለን ልንቀበለው አይገባንም። መንፈስ ሰይጣን ያደረባቸው ቢጽሐሳውያን ሳይበቁ በቅተናል፤ ሳይጸድቁ ጸድቀናል፤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሳያድርባቸው አድሮብናል በማለት በርኩስ መንፈስ ሊያቁራኙን ስለሚችሉ መጠንቀቅ ይገባናል።

ሰይጣንም ለማሳሳት መንፈሳዊ መልአክን ተመስሎ ስለሚመጣ ልጆቹ አሳሳቾችም ሐዋንን እንዳሳተ እባብ ማደሪያው በመኾን የማያታልሉት ማታለል ስለሌለ ክርስቲያን ሁሉ ሊጠበቅ ይገባዋል። (፪ኛ ቆሮ.፲፩፥፩–፫፤ ፲፫–፲፭) በሙሴ ላይ አድሮ የነበረ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአንብሮተ ዕድ ለኢያሱ ሊሰጥ የቻለው ሙሴ እውነተኛ ነቢይ የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት በመኾኑና ኢያሱም በረከቱን ለመቀበል የእግዚአብሔርን ነቢይ በአክብሮት ተቀብሎ ይመላለስ ስለነበር ነው።

ኢያሱ ሙሴን ሲያከብር ጌታዬ ሙሴ እያለ ነበር ሙሴ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ስላደረበት የጸጋ ጌትነት ነበረውና በዚህ ምክንያት ጌታዬ እያለ ያከብረው ነበር። በቅዱስ ወንጌል «ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል። (ማቴ.፲፥፵፩) ተብሎ መነገሩ ነቢያትን በሚያከብሩ ሰዎች ላይ እንደ ዋጋ ሆኖ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ስለሚያድርና የረድኤታቸው የበረከታቸው ተሳታፊ ስለሚያደርግ ነው። በቅዱሳን እጅ መጫን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ መታደሉን ለማስረዳት ብንገልጽም ነፋስ ከምን ተነስቶ ወደየት እንደሚደርስ ለማወቅ እንደሚያዳግተን በዚሁ አንጻር መንፈስ ቅዱስ ረድኤቱ ጸጋው እንዴት እንደሚያድር ለማወቅ እንቸገራለን።

በኤልያስ አድሮ የነበረው መንፈስ ረድኤት ለኤልሳዕ ዕጥፍ ድርብ ሆኖ በነቢዩ መጎናጸፊያና በመልኩም እይታ ተሰጥቶታል። እንዴት እንደሚተላለፍ ግን አኳኋኑን እንደ ግዙፍ ነገር ማስረዳት ጥልቅነቱን ማወቅ አይቻልም በእምነት የሚታወቅ እንጂ በሥጋዊ አእምሮ ምርምር የሚከሰት አይደለምና። (፪ነገ.፪፥፮–፲፭) መንፈስ ቅዱስ አድሮ ሥራ ሲያሠራ እንጂ ከአንዱ ቅዱስ ነቢይ ወይም ሐዋርያ ወይም ጻድቅ ረድኤቱን ሀብቱን ከፍሎ ሲያሳድር አይታወቅም። የነፋስ ጉዞ አቅጣጫ ያለመታወቅ ሁኔታ ለመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ መኾኑ ስለዚህ ነውና ሐተታው ሁሉ ለዚህ በማስረጃነት መጠቀሱን ተገንዝበን ለማስተዋል እንሞክር (ዘኁ.፲፩፥፳፬–፴፤ ዮሐ.፲፥፵፩–፵፭፤ የሐዋ.፱፥፲፯–፲፰) በበዓለ ሃምሳም በጽርሐ ጽዮን ሳሉ በመቶ ሃያው ቤተሰብ መንፈስ ቅዱስ ሲያድር መድኀኒታችን ስለ መንፈስ ቅድስ አሰጣጥ በነፋስ መስሎ በተናገረው መሠረት መኾኑን ማስተዋል ይገባል። በግብሩ ሐዋርያት ምዕ.፪ ከ፩ እስከ ፬ ያለውን ንባብ ብንመለከት መንፈስ ቅድስ በወረደላቸው ጊዜ ድምፁን በአምሳለ ዓውሎ ነፋስ አሰምቶ እንደ ነበር ተጽፎ ይገኛል በተለይም «ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ...በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች የናገሩ ጀመር» ያለውን ሐረግ እንመልከት በግልጽ መንፈስ ቅድስ



www.ethiopisnorthodox.org

በአምሳለ ነፋስ በዓውሎ ነፋስ አርአያ መሰጠቱን ያመለክተናል። በግዕዙም ያለው ንባብ ተመሳሳይ ነው። ግብረ ሐዋ ምዕ ፪ ቁ ፪ትን ብቻ ብናይ «መጽአ ግብተ እምሰማይ ድምፅ ከምድምፅ ነፋስ ዓውሎ» ሲል ይገኛል። ትርጉሙም ከወደ ሰማይ እንደ ዓውሎ ነፋስ ያለ ድምፅ ነጐዶ ተሰማ ማለት ነው። በዓውሎ ነፋስ የተመሰለው መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ የቤተክርስቲያን መምህራን መንፈስ ቅዱስ እንዴት በነፋስ እንደሚመሰል በአንድምታው ሲተነትኑት ምሥጢሩ ደስ ያሰኛል። ከዚህ ቀጥሎ ነፋስ ለመንፈስ ቅዱስ ምሳሌነቱ እንዴት እንደኾነ እንመለከታለን።

ነፋስ በዓይን አይታይም ረቂቅ ነው፤ በተፈጥሮው ከ፬ቱ ባሕርያት አንዱ ቢኾንም እንደ ውሀ ወይም እንደ መሬትና እሳት አይታይም፤ የማይታይ ረቂቅ በመኾኑ ለመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሆኗል። ነፋስ ረቂቅ እንደኾነ መንፈስ ቅዱስም ረቂቅ ነውና። በመንፈስ ቅዱስ ረቂቅነትና በነፋስ አለመታየት መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ። መንፈስ ቅዱስ የነፋሳት ፈጣሪ ስለኾነ ርቀቱ በዚያው መጠን በፈጣሪና በፍጡር መካከል ያለውን ልዩነት ያሕል ነው።

ነፋስ ኃያል ነው ከኃያልነቱም የተነሣ ቤት እስከማፍረስ ማዕበል እስከ ማንሳት መርከብ እስከመገልበጥና የምድርን ትቢያ እስከመጠራረግ ይደርሳል። መንፈስ ቅዱስ እንደነፋስ ኃያል ነው። ከኃይሉም የተነሳ ሰማያትና ምድርን ያናውጻል ከኃጢአታቸው ከክህደታቸው የማይመለሱትን ይቀሥፋል።

ዓመፀኞችን፥ መናፍቃንንና አጋንንትን ጣዖት አምላኪዎችን ፈርዶ ያጠፋቸዋል እንደትቢያ ይጠርጋቸዋል። እንደ ዛፍ ይነቃቅላቸዋል። ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ ብሏል «ከፉዎች ግን እንዲህ አይደሉም ነገር ግን ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው ትቢያ ናቸው።» (መዝ.፩፥፬) ነፋስ ኃያል እንደመኾኑ ትቢያን ጠራርጎ እንደሚወስደው በነፋስ የተመሰለው መንፈስ ቅዱስም በኃጥአን በአጋንንት ፈርዶ ሊቀጣና ሊኮንን የሚችለው ኃያል አምላክ መኾኑን ያመለክታል።

ስለዚህም መንፈስ ቅዱስን ሊዳፈሩ የሚሞክሩ ሁሉ መቀሠፋቸው የማይቀር ነው። የነፍስ ቅጣት የሥጋ መቅሠፍት እንዳይደርስብን መንፈስ ቅዱስንና ሥራውን እንደ ቤተ አይሁድና መናፍቃን ከመቃወም እንጠበቅ በቅዱስ ጴጥሮስ አድሮ ሐናንያንና ሰጲራን እንደ ቀሠፈ እንዳይቀሥፈን በቅዱስ ጳውሎስ አድሮ በረያሱስ የተባለውን ጠንቋይ አስማተኛ የሐሰት ነቢይ እንዳሳወረው እንደቀጣው እንዳይቀጣን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ከማስተባበል ወይም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎችን ቅዱሳንን ከመቃወም እንጠበቅ (የሐዋ. ምዕ.፭ ቁ.፩–፲፩ የሐዋ ሥራ ፰፥ ቁ.፺፩–፺፫ የሐዋ.ሥራ ፲፫ ቁ.፩–፲፪) በሌላ ቦታም መዝሙናው ዳዊት ስለ መንፈስ ቅዱስ ኃያልነት ሲገልጽ «በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ» ይላል (መዝ.፴፪፥፮) ቃል የተባለው ወልድ ነው ወልድ የእግዚአብሔር አብ ቃል ነው። እስትንፋስ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ነው መንፈስ ቅድስ የእግዚአብሔር ቅዱስ እስትንፋስ ነውና። ቃል የተባለ ወልድና እስትንፋስ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ለአብ ቃልና ሕይወት በመኾን በሕልውና ከአብ ሳይለዩ ሥራ እንደሚሠሩ በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርታችን በሰፊው ስለተገለጸ ሐተታ አያስፈልገውም።

ነቢየ እግዚአብሔር እንደተናገረው እግዚአብሔር አብ በቃሉ በወልድ ሰማያትን እንደ አፀና በእስትንፋሱ በመንፈስ ቅዱስም ሠራዊታቸውን አፅንቷቸዋል። ማካፈል አይደለም ሁሉም በሁሉ አሉ። አብ በቃሉ፤ በወልድና በእስትንፋሱ በመንፈስ ቅዱስ ሰማያትንም ሠራዊታቸውንም እንደሚያፀናቸው ወልድና መንፈስ ቅዱስም እንደ አብ ይሠራሉ ያፀናሉ፤ ይኸም ማለት በህልውና ስለሚገናዘቡ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተለያይተው የሚሠሩት ሥራ የለም ማለት ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና እንደ ወልድ ሰማያትንና ሠራዊታቸውን በኃይሉ ያፀናቸዋል። ጥንቱንም ሰማያትን ከነሠራዊታቸው ጠቅላላውን ፍጥረት የፈጠረ አምላክ ስለኾነ ይኸን ይሠራል ያንን አይሠራም አይባልም። ሰማያትን ከነሠራዊታቸው የሚያፀናቸው ኃያል አምላክ ነው። ዝርው መንፈስ ወይም ዝርው ኃይል ፍጡር ቢኾን ኑሮ ይኸን ማድረግ ባልተቻለውም ነበር። የፍጥረታት አስገኝ አካላዊ ባሕርያዊ መንፈስ ስለኾነ የአብና የወልድ እስትንፋስ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ማድረግ ይችላል በዚህም ሁሉን ቻይ ከሃሌ ኵሉ ይባላል። በውጭው ቋንቋ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ እግዚአብሔር እንደ መኾኑ (Omnipotent) አምኒፖቴንት ይባላል ሁሉን ቻይ ኃያል አምላክ እንደማለት ነው። ነፋስ ኃያል እንደኾነ መንፈስ ቅዱስም ኃያል ነው ብለናል። ነፋስ ኃያል ቢባልም ዝርው ኃይል ፍጡርና ውሱን ነው መንፈስ ቅዱስ ግን እንዲህ አይደለም የማይወሰን መለኮታዊ አካል ያለው ኃያል ፈጣሪ ነው። ፈጣሪ ስንል ከወልድና ከአብ ተለይቶ ብቻውን ፈጣሪ ነው ማለታችን አይደለም ከወልድ ከአብ ሳይለይ ሁሉን ያስገኘ ፈጣሪ መኾኑን መግለጻችን ነው እንጂ። በእግዚአብሔርነትም ሦስቱም አካላት አብ፤ ወልድ፤ መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው። እግዚአብሔር ሁሉን የሚችል አምላክ እንደኾነ ታጋሹ ኢዮብ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል «ሁሉን በሚችል አምላክ ዘንድ ያለውን አልሸሽግም» (ኢዮ. ፳፯፥፲፩) ሁሉን የሚችል አምላክ በመንፈሱ ለሰማያት ፅንዓትን ውበትን ሰጥቷል። ሰማያትን ያፀናቸው በውበት ያስጌጣቸው ሁሉን ቻይ አምላክ በመንፈሱ እንደኾነ ተነግሮዋል። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ



www.ethiopisnorthodox.org

ሁሉን የሚችል አምላክ ይባላል። (ኢዮ.፵፮፥፲፫)

ሁሉን ቻይ ኃያል መንፈስ ቅዱስ ሰማያውያን ኃያላት መላእክትን በቦታቸው በአገልግሎታቸው በቅድስና እንደአፀናቸው ነቢያትን በትንቢት ሐዋርያዕትን በስብከት ሰማዕታትንና ጻድቃንን በተጋድሎ አፅንቷቸዋል። ይኸውም ኃይሉን በማሳደር ጸጋውን በማደል ነው።

እኛንም በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልነውን መንፈስ ቅዱስ በኃይሉ አፅንቶን ስለ ሃይማኖት የሚመጣብንን ፈተና በትዕግሥት ለመቋቋም ያስችለን ዘንድ በሃይማኖት ጸሎት ልንማፀነው ይገባናል። በተሽከርካሪ መኪናዎች ጐማዎች የሚሞላው የነፋስ መጠን ግዙፉን ጭነት ሊሸከመው እንደሚችል ዘመናዊውን የቴክኔዎሎጂ ጥበብ ብናስተውል እንረዳለን። የማይታየው ነፋስ ግዙፉን ተሽከርካሪ የመሸከም ኃይል ካለው፥ መንፈስ ቅዱስማ በሰውነታቸው ካደረ በመከራ ጊዜ ግዙፉን እኛን ምን ያሕል በትዕግሥት ያፀናን ይሆን? ፍርሃትን አጥፍቶ ቅዱስ ድፍረትን፥ ጥርጥርን አጥፍቶ ፍጹም እምነትን በመለገስ በገድል በትሩፋት ማለትም በክርስቲያናዊ ሕይወት በበጎ ሥራ ሁሉ እንድንተጋ እንድንፀና እሱ መንፈስ ቅዱስ በኃይሉ ይርዳን። መድኀን ክርስቶስ ከዕርገት በፊት ለቅዱሳን ሐዋርያቱ ከላይ ኃይል እስከትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ቆዩ (ሉቃ.፳፬፥፵፱) ካላቸው በኋላ መንፈስ ቅዱስን በዓውሎ ነፋስ አምሳል ልኮላቸው የመንፈስ ቅዱስን ኃይል አልብሷቸዋል። ዓውሎ ነፋስ ኃያል እንደኾነ መንፈስ ቅዱስም ኃያል ነው። ኃያል መንፈስ ቅዱስ ኃይሉን ያልብሰን፤ የኢየሩሳሌም አምሳያ በኾነች በቤተክርስቲያን ያፅናን በክርስቲያናዊ ተግባር እንድንፀና ኃይል ይሁነን። በእምነትና በእውነት ከቤተክርስቲያን ጉባኤ ከቅዳሴ ሳንለይ ሐዋርያት አባቶቻችንን መስለን ሁል ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመጠበቅ በቤተ መቅደሱ እንትጋ። አንድ ልብ አንድ ነፍስ ይኑረን። እንደ አንድ ልብ መካሪ፤ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሁነን በጾም በስግደት፤ በጸሎት እንጽና፤ ደጅ ጥናታችንን አናቋርጥ። ለዚህም መንፈስ ቅዱስ ይርዳን በሐዋርያት ጉባኤ ተገኝታ ጸሎታቸው እንዲያርግ ምክንያት የሆነች የአምላካችን የአማኑኤል እናቱ ድንግል ማርያም ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እንዳይለየን ዘወትር የቀደመ የምሕረት ቃል ኪዳኗን ታሳስብልን ታማልደን አሜን። (ሉቃ.፳፬፥፵–፵፫፤ የሐዋ.፩፥፲፪–፲፬፤ የሐዋ.፪፥፵፫–፵፯)

ሌላው የነፋስ ጠባይ በምልዓት መገኘት ነው ነፋስ በሁሉ ቦታ በዓለም ዙሪያ ከጽንፍ እስከ አጽናፍ በምላት ይገኛል። በሁሉ ቦታ ማለትም በምላት ሳለ መኖሩ የሚታወቀው ባሕር ሲገሥፅ ዛፍ ሲያናውጥ ነው። መንፈስ ቅዱስም እንደነፋስ በምልዓት ይገኛል። መንፈስ ቅዱስ የሌለበት ሥፍራ አይገኝም፤ በምድርና በሰማይ ከዚህም በታችና ከዚያም ባላይ በሁሉ ቦታ በምልዓት ይኖራል። መንፈስ ቅዱስ በምልአት ሳለ መኖሩ አይታወቅም። መኖሩ የሚታወቀው ትንቢት ሲያናግር ምሥጢር ሲያስተረጉም ገቢረ ተአምራት ወመንክራት ሲያሠራ ገድል ትሩፋት ሲያስፈጽም ነው። ነፋስ ዛፍን እንደሚያናውጥ ባሕርን እንደሚገሥፅ መንፈስ ቅዱስም በዛፍና በባሕር የተመሰሉትን ፍጥረቶቹን የሰዎችን ልጆች በቤተ ክርስቲያን አድሮ መምሕራንን ልኮ ይመክራል ይገሥጻል። በሰው ልጆች ላይ አድረው የሚያስቱ ርኩሳን መናፍስትንም ያናውጣቸዋል። ያርቃቸዋል። ሰዎችን በንስሐ እየገሠፀ ከኃጢአታቸው ተመክረው እንዲመለሱ ያደርጋቸዋል የነፋስ መኖሩ፤ በሥራው እንደታወቀ የመንፈስ ቅዱስ ሕልውናው በግብሩ ይታወ ቃል። በነፋስ ምልአትነት ጉድለት አለበት በቦታና በጊዜ ይወሰናል፤ ሕፁፅ ነው በመንፈስ ቅዱስ ምልአ ትነት ግን ጉድለት የለም መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ጊዜና ቦታ ለመኖር የሚችል በቦታና በጊዜ የማይወሰን ምሉዕ በኵለሄ ነው። ምሉዕ በኵለሄ ማለትም በሁሉም ቦታ በማንኛውም ጊዜ በቦታና በጊዜ ሳይወሰን በሁሉ ቦታ መኖር የሚችል ማለት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ወይም መንፈስ ቅዱስ የሌለበት ቦታ አይገኝም። በሁሉም ቦታና ጊዜ ያለና የሚኖር ነው። ዳዊት እንዲህ ሲል ይዘምራል «አይቴኑ አሐውር እመንፈስከ ወአይቴ አጐይይ እምቅድመ ገጽከ እመኒ ዐረጉ ውስተ ሰማይ ህየኒ አንተ ወእመኒ ወረድኩ ውስተ ቀላይ ህየኒ ሀሎከ» (መዝ.፻፴፰፥፯–፰) ትርጉሙም ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ ወደሲኦልም (ጥልቁም) ብወርድ በዚያ አለህ» ማለት ነው መንፈስ ቅዱስ በሁሉ ቦታ የሚኖር፤ ያለ ምሉዕ በኵለሄ መኾኑን የሚያስረዳ ገጸ ንባብ ነው። ስለዚህ የነፋስ ምልዓት ጉድለት ቢኖረውም ለመንፈስ ቅዱስ ምልዓት በምሳሌነት ያገለግላል። ስለኾነም መንፈስ ቅዱስ በነፋስ ምልዓት ይመሰላል።

ነፋስ ፍሬውን ከገለባው ይለያል ፍሬው ተለይቶ በጎታ በጎተራ መቀመጥ እንዲችል በነፋስ ከገለባ መለየት ይኖርበታል እንደ ስንዴ እንደ አጃ ገብስ የመሳሰሉ የእህል ፍሬዎች ከገለባ ተለይተው በጎተራ የሚቀመ ጡት ገበሬው በነፋስ አማካይነት ፍሬውን ከገለባ መለየት ሲችል ነው። (ማቴ.፫፥፲፪)

ነፋስ ፍሬውን ከገለባ እንደሚለይ መንፈስ ቅዱስም ጻድቃንን ከኃጥአን ምዕመናን ከመናፍቃን ይለያቸዋል። ፍሬው በነፋስ አማካይነት ከገለባ ከተለየ በኋላ በረቅ በጎተራ እንደሚቀመጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ቅዱሳን ከርኩሳን ተለዩ በኋላ በረቅ በጎተራ በተመሰሉ በገነት በመንግሥተ ሰማያት እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል፤ ገለባው በእሳት እንደሚቃጠል ኃጥአን ርኩሳን በሲኦል በገሃነመ እሳት በማይጠፋ እሳት ይቀጣሉ።

ነፋስ መንቅሒ ነው ሙቀት ወበቅ ያደበተውን ያፈዘዘውን ሰውነት ነፋስ ሲነፍስ ያነቃቃዋል ትጋትን፤ ንቃትን ይሰጠዋል መንፈስ ቅዱስም መንቅሒ ነው በዓለም ፍቅር ሙቀት በኃጢአት ወበቅ በሰይጣናዊ ፈተና የደከመ

www.ethiopisnorthodox.org

ችውን በጥርጥር የፈዘዘችውን ሰውነት መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ፍቅር እንድትነቃ ትንሣኤ ሕሊና እንዲኖራት ያደርጋል። የሰይጣንን ጾር (ፈተናውን) በትዕግሥት በትሕትና በእምነት አሸንፋ ለበጎ ሥራ ሁሉ የነቃች የተጋች ያደርጋታል።

ነፋስ በጎውን መዓዛ ሁሉ ያመጣል፤ የዝባድም ሆነ የሽቱ የአበባዎችን ሽታ እያመጣ ሰውነትን ደስ ያሰኛል፤ መንፈስ ቅዱስም መዓዛ ገነትን ተስፋ መንግሥተ ሰማያትን ጣዕመ መስቀልን ወደ አማኝ ነፍስ እያመጣ በተስፋ ደስ ያሰኛል። የዓለምንና የኃጢአትን መጥፎ ሽታ ያርቃል የገድል የትሩፋትን አበባዎች የመዓዛ ጣዕም እያሰማ ውስጣዊ ሰውነትን ያረካል የቅዱሳንን ገድል ትሩፋት ለምዕመናን እንዲጥማቸው መዓዛ ቅዱሳንን እያሰቡ እንዲመሰጡ ያደርጋል።

መንፈስ ቅዱስ በነፋስ የተመሰለበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ሰዎች ከእግዚአብሔር ፈቃድ ተለይተው የባቢሎንን ግንብ (ጥቅመራግውን) ባነፁ ጊዜ ግንባቸው የፈረሰባቸው በነፋስ ነበር። (ዘፍ.፲፩፥፩—፱) ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነፋስ ለመዓት እንጂ ለምሕረት እንደተፈጠረ የማያውቁ ሰዎች ነበሩ። መንፈስ ቅዱስ በነፋስ አምሳል በመሰጠቱ ነፋስ ለምሕረትም፣ እንደተፈጠረ ሊታወቅ ተችሏል። በሌላም በኩል ነፋስ የመዓትም የምህረትም መገለጫ ስለኾነ ለስነ ፍጥረት ፬ት የምሕረት ነፋሳትና ፫ት የመዓት ነፋሳት እንዳሉ ታውቋል። አንድ ነፋስ የምሕረትም የመዓትም መገለጫ መኾን እንደሚችል መንፈስ ቅዱስም በቁጣው ንስሐ የማይገቡትን ሲቀጣቸው በምሕረቱ ተነሳሕያንን (ንስሐ የሚገቡትን) ሲያድናቸው ሲጠብቃቸው መኖሩን ያመለክታል።

አንዱ ነፋስ የመዓትም የምሕረትም መገልገያ ሆኖ ዓመፀኞች ሲቀጡበት የጽድቅ ሰዎች ሲጠቀሙበት ይገኛሉ። መንፈስ ቅዱስም ዓመፀኞችን የሚቀጣ ቅኖችን ታዛዦችን የሚያድን ፍርድም ምሕረትም በእጁ ያለ አምላክ መኾኑን ዐውቀን መንፈስ ቅዱስን ከማሳዘን እንጠበቅ። የስናዖር ሰዎች የኃጢአት ግንብ መገንባታቸው አልጠቀማቸውም። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ተለይተን ያለ መንፈስ ቅዱስ መሪነት በሥጋዊ አምሮታችን የምንገነባው የዓመፅ ካብ በተናደ ጊዜ የገዛ ሥራችን እኛኑ እንዳያጠፋን እንጠንቀቅ። ከፈጣሪ ቃል ፈቃድ ውጭ የሚገነባ ሰይጣናዊ ሥራ ሁሉ በእኛ ዘንድ ምናልባት እንደ ሥልጣኔ ተቆጥሮ ቢታይም የኋላ የኋላ የባቢሎን ግንብ ከመሆን አይዘልም።

መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደ መሆኑ በኃጢአት እልከኝነት በክህደት እብሪት የሚጓዙትን በመዓቱ ይገሥጻቸዋል። የኃጢአት ካብ ሥልጣኔያችንንም ያፈርሰዋል። የሕይወታችንንም ሕንፃ በመቅሠፍቱ ይንደዋል። ነፋስ በመጠኑ በነፈሰ ጊዜ ለሰውም ለእንስሳትም ለዕፅዋትም ሕይወት ይሆናል። ከልኩ ሲያልፍ ግን የቁጣ ምልክት ነው። ሰውን ከአደጋ ላይ ይጥለዋል። የእንስሳትን ሕይወት ይቀጫል ዕፀዋትንም ከሥራቸው ይነቅላቸዋል፤ ወይም ቅጠላቸውን በማጠውለግ ያለ ፍሬ ያስቀራቸዋል። መንፈስ ቅዱስን በትሕትና ሳይዳፈሩ በእምነት ለሚቀበሉት ሕይወተ ሥጋቸውንም ሕይወተ ነፍሳቸውንም ጠብቆ ከፍሬ ትሩፋት ከፍሬ ክብር ያደርሳቸዋል። የሚዳፈሩትን ግን በነፍስ በሥጋ ይቀጣቸዋል።

መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ሰጭ አዳኝ እንደመኾኑ ያመኑበትን ያድናቸዋል። በአንጻሩ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ፈታሒ ነውና በትክክል ፈርዶ ዓመፀኞችን ይቀጣቸዋል።

ሐናንያና ሰጲራ የተቀጡት መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸውን ሐዋርያትንና ራሱን መንፈስ ቅዱስን ለማታለል ስለሞከሩ ነበር። ዛሬም ለሰው ይምሰል እንደእነ ሐናንያና ሰጲራ መንፈስ ቅዱስን የምናታልል የእግዚአብሔርን ሰዎች ለማሞኘት የምንሞክር እንኖር ይሆናል። እንጠንቀቅ በቅዱስ ጴጥሮስ አድሮ በነሐናንያ የፈረደ አምላክ እሱ መንፈስ ቅዱስ ሊፈርድብን ይችላል። እነዚያ የእግዚአብሔርን መንፈስ እንደተፈታተኑት እንፈታተነን፤ በመፈታተናችንም ለመቅሰፍት እንደተዳረጉ እኛም እየተደፋፈርን ሕይወታችንን እና ስቀጫት።

መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ንዋያትና ቅዱሳንንም እናክብር የቅዱስ ጴጥሮስንና የቅዱስ ዮሐንስን ጥላቸውን ሳይቀር የጥንት ክርስቲያኖች በማክበራቸው በነፍስ በሥጋ ተጠቅመዋል ተፈውሰዋል።

እንደ እነ ሐናንያ ያሉት ግን በመናቃቸው በማታለላቸው ተቀሥፈዋል። ዛሬም ያ መንፈስ በቤተ ክርስቲያን አድሮ ምሕረት የሚገባቸውን ሲምር ቅጣት የሚገባቸውን ሲቀጣ ይኖራል (የሐዋ.፭፥፲፪—፲፮) የመንፈስ ቅዱስ ፍሬው በውስጣችን ሳይኖር በአፋችን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተናል ብለን የምንዋሽ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ሳይቀጣን ቶሎ ከትዕቢታችን እንመለስ። ልባችንን በኃጢአትና በጥርጥር አደንድነን እልከኛ አናድርገው፤ ሐናንያና ሰጲራ የጌታን መንፈስ እንደተፈታተኑት አንፈታተን። የመንፈስ ቅዱስ መቁረጫ ሥልጣኑ ፍርዱ የንስሐ ፍሬ ካላፈራን ቆርጦ ለእሳት እንደሚዳርገን ዐውቀን ንስሐ እንግባ፤ እንደ እነ መቅዶንዮስና የዘመኑ አርዮሳውያን መንፈስ ቅዱስን ፍጡር ከማለት እንጠበቅ። አጽናፊ ጰራቅሊጦስ ተብሎ የሚጠራውን መንፈስ ቅዱስን ከፍጡር ጋር አናመሳስለው። ያውም ከሐሰተኛ ነቢይና ከመሰሎቹ ጋር አናወዳድረው። አይሁድ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ለሰይጣን ሰጥተው ከሰይጣን ተግባር ጋር አመሳስለው በመገኘታቸው ተፈርዶባቸዋል። እኛም እንደ እነርሱ እንዳይፈረድብን እንጠንቀቅ። ክርስቲያኖች ሆይ ቅዱስ ጳውሎስ የመከረንን አባታዊ ምዕዳን ሰምተን እንመክር እንገሠጽ። ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዳናሳዝነው ከኃጢአት ሥራ እንድንቆጠብ። አታሳዝኑት ብሎ መክሮናልና አጽናኙ መንፈስ በውስጣችን ያለውን የሥጋን ርኩሰት ሁሉ በንስሐ እንድናስወግደው ይርዳን። ሰውነታችንን በንጽሕና በቅድስና ያጌጠች ያድርግልን። አሜን (ኤፌ.፬፥፴—፴፪) ✢

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

# ዓምደ-ሃይማኖት

ካሣሁን፡ ገ/ክርስቶስ

## መንፈስ ቅዱስና ምሳሌዎቹ

### መንፈስ ቅዱስ በቅብዓ ዘይት ስለመመሰሉ

መንፈስ ቅዱስ በቅብዓ ዘይት ይመሰላል። በዘመን አበው ለነበረው ለያዕቆብ በኋላ ጊዜ ቤቴል (ቤተ እግዚአብሔር) ተብላ በተጠራችው በሎዛ እግዚአብሔር ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ከሰማይ ወደ ምድር በተተከለች መሰላል ተገለጸለት። ያዕቆብም ማልዶ ተነሣና ተንተርሶት የነበረውንም ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድርጎ አቆመው፤ በላዩም ዘይትን አፈሰሰበት፤ ስፍራውንም ቤቴል ብሎ ጠራው ቤቴል ማለትም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው። (ዘፍ.፳፰፥፲-፳፪)

ያዕቆብ የቀሳውስት ምሳሌ ሲኾን ደንጊያው የአሕዛብ ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነበር። በምሳሌያዊ ትንቢት የቆየው የያዕቆብ አሠራር፤ በኋላ ጊዜ በሐዲስ ኪዳን ዘመን ፍጻሜውን አገኘ። በሐዲስ ኪዳን በቀሳውስት፣ በቤተክርስቲያን አባቶችና በያዕቆብ ወገኖች በሐዋርያት እጅ በዘይት የተመሰለው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ይታደል ጀመር። ለምሳሌ የሰማርያ ሰዎች በወንጌል ባመኑ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ እንዲያገኙ ከሐዋርያት መካከል ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ሄደው በአንብሮተ ዕድ (እጃቸውን በመጫን) የጸጋ መንፈስ ቅዱስ ተሳታፊዎች አድርገዋቸዋል። (የሐዋ.፰፥፲፬-፲፯)

ሰው እየበዛ ሲሄድ ግን በእጅ መጫን ፈንታ ሐዋርያት ሜሮንን አፍልተው (ሜሮን በጸሎት የከበረ ዘይት ነው) በየሀገረ ስብከቱ ለተሾሙት ጳጳሳት ቀሳውስት በማካፈል ምዕመናንን በሜሮን እየቀቡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እንዲታደላቸው ያደርጉ ነበር። ይኸንን በቅብዓ ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ተሳታፊዎች መኾናቸውን በመልእክታቸው ይገልጹ እንደነበር ጽሑፎቻቸው ያስረዳሉ።

ቅዱስ ዮሐንስ «እናንተም ከቅዱስ ቅባት ተቀብላችኋል ሁሉንም ታውቃላችሁ...እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፤ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ እውነተኛም እንደሆነ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ» በማለት ምዕመናንን በሜሮን (በቅብዓ ዘይት) የተቀበሉት መንፈስ ቅዱስ ከሣቴ (ምሥጢር ገላጭ) መምህር አስተማሪ መኾኑን ይገልጽላቸዋል። (፩ዮሐ.፪፥፳ና ፳፯)

ቅዱስ ጳውሎስም በተመሳሳይ መልኩ ሲያስረዳ በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው።» ብሎ ይገልጻል (፪ቆሮ.፩፥፳፩) በመንፈስ ቅዱስ ዘይትነት ምእመናን በክርስቶስ አምነው እንዲከብሩ እንዲጸኑ እግዚአብሔር አብ በቸርነቱ የሚቀባቸው መኾኑን ያስረዳል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ደብተራ ስምዕ (የምስክርነት ድንኳን) ንዋየ ቅድሳት ካህናት ነቢያትና ነገሥታት በዘይት ተቀብተው ይከብሩ፤ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ይቀድሱ (ይለዩ) እንደነበር ተጽፏል። (ዘጸ.፴፥፳፪-፴፪) ነቢዩ ሳሙኤል ሳኦልንና ዳዊትን በቅብዓ ዘይት ቀብቶ ሀብተ መንግሥትን አሳድርባቸዋል። (፩ሳሙ.፲:፩፤ ፩ሳሙ.፲፮፥፲)

ነቢዩ ኤልያስም ኢዩን ለንጉሥነት ኤልሳዕን ለነቢይነት በቅብዓ ዘይት ቀብቶ ሀብተ መንግሥት፣ ሀብተ ትንቢት እንዲያሳድርባቸው እግዚአብሔር አዝዞታል። (፩ነገ.፲፱፥፲፮) በሐዲስ ኪዳን ዘመንም ልጅነት ሀብተ መንፈስ ቅዱስ በቅብዓ ሜሮን በአንብሮተ ዕድ ይታደል እንደነበር ተገልጿል። ምዕመናንና ቀሳውስት የሚከብሩት፤ ልዩ ልዩ የኾነውን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ የሚቀበሉት በልጅነት ከብረው ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰማሩት በአንብሮተ ዕድ ወይም በሜሮን አማካይነት መንፈስ ቅዱስ ሲያድርባቸው ነው። (፩ቆር.፩፥፲፩፤ የሐዋ.፲፫፥፩-፫) በብሉይም በሐዲስም ዘይት ለመንፈስ ቅዱስ ምሳሌው ሆኖ የመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ሀብተ ጸጋ መቀበያ በመኾን ሲያገለግል ይገኛል። የሐዲስ ኪዳን ካህናት ሐዋርያትና ቀሳውስት ሕሙማንን ለማዳን ቅብዓ ቅዱስ ቀብተው የሃይማኖት ጸሎት ጸልየው ፈውስ ሥጋዊ ፈውስ መንፈሳዊ እንዲቀበሉ ያደርጋሉ። በዘይት መቀባታቸውም ዘይት ምሳሌነቱ ለመንፈስ ቅዱስ ስለኾነ ነው (ማር.፯፥፲፫፤ ያዕ.፭፥፲፬-፲፭)

በመዝሙረ ዳዊት «ወይን ያስተፌስሕ ልበ ሰብእ ወቅብዕ ለአብርሆ ገጽ እክል ያፀንዕ ኀይለ ሰብእ» (መዝ.፻፫፥፲፭) ተብሎ በሰም ለበስ ቅኔ ትንቢት ተነግሮዋል። ቃል በቃል ጥቅሱ ሲተረጎም «ወይን የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል ዘይትም ያበራል እህልም የሰውን ጉልበት ያጠነክራል» ተብሎ ነው። ምሥጢራዊ ፍቺ ግን እንደሚከተለው ነው። ወይን ለደሙ እህል ለሥጋው ምሳሌ በመኾን የክርስቶስን ሥጋ ደም ያመለክታሉ። ወይን ልብን





www.ethiopisnorthodox.org

ደስ እንደሚያሰኝ እህልም ጉልበትን እንደሚያጠነክር የክርስቶስ ሥጋና ደም የክርስቲያንን ነፍሳዊ ልብ ደስ ያሰኛል። የነፍሱንም ጉልበት ያፀናለታል።

ዘይት የሰውን ፊት እንደሚያበራለት በዘይት የተመሰለው መንፈስ ቅዱስም ሰውን ብሩህ መልአክ ያስመስለዋል። ለዚህም መረጃው መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳን ላይ የፈጸመው ሥራው ነው። ለምሳሌ አባቶቻችን ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ከተቀበሉ በኋላ የሚደርስባቸውን መከራ ሁሉ በፍጹም ደስታ ሹመት ሽልማት እንደተሰጠው ሰው በብሩህ ገጽ በፍቅር ይቀበሉት ነበር። ቅዱስ እስጢፋኖስም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ስለኾነ በሰማዕትነት መድረክ ላይ ሳለ ማንኛውንም የደረሰበትን ፈተና በፈገግታ በፍቅር በደስታ ፊቱ ብሩህ መልአክ መስሎ ተቀብሎታል። (የሐዋ.፭፥፵—፵፪፣ ምዕ.፮፥፲፭ና ምዕ.፯፥፶፱—፷)

በዘመነ መንኮሳትም አበው ጻድቃን መከራውን ሁሉ በደስታ ይቀበሉት ነበር። ዮሐንስ ሐጺር ከወንድሞቹ አንዱ ለፈተና ቢሰድበው ፊቱን ሳይቋጥር በደስታ በብሩህ ገጽ እንደተቀበለው በዜና አበው ተጽፏል። ይኸ የኾነው በዘይት የተመሰለው መንፈስ ቅዱስ ልቡን በፍቅር ስለሞላው በደስታ እንዲቀበለው በማድረጉ ነው። ጌታ (በሉቃስ ወንጌል ምዕ ፲፥ ፴፫—፴፬) ላይ

በምሳሌ የገለጸው ርኅሩኅ ሳምራዊ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ሰው ከአደረገለት ችሮታዎች አንዱ በቁስሎቹ ላይ ዘይትና የወይን ጠጅ ማፍሰሱ ነበር፣ ሳምራዊ የክርስቶስ ምሳሌ ሲኾን ወንበዴዎች አጋንንት ናቸው። በወንበዴዎች እጅ የወደቀው ሰው የአዳም ምሳሌ ነው። ቁስሉ በአዳም የደረሰበት መከራ ፍዳ ነው። ወይኑ የደመ ክርስቶስ ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። ክርስቶስ በደሙ ክሶ መንፈስ ቅዱስን ለአዳም መስጠቱን መናገር ነው። ሥጋወደሙ ልጅነት (ሀብተ መንፈስ ቅዱስ) ለአዳም ዘር ሁሉ አምኖ ከተገኘ በወንጌል ከተመራ የማይነፈገው መኾኑን ድኅነት ጸጋ ለሁሉ መናኘቱን መሰጠቱን ያመለክታል። መንፈስ ቅዱስ በቅብዓ ዘይት መመሰሉን አይተናል። ቀጥለን መንፈስ ቅዱስ በውኃ መመሰሉን እንመለከታለን።

ሸ. መንፈሳዊ ቅዱስ በውኃ ስለመመሰሉ፣

በጥንተ ፍጥረት መንፈስ ቅዱስ በውኃ ላይ አድሮ ተገልጿል። መንፈስ ቅዱስ በፈጣሪነቱ የነፋስም የመሬትም የእሳትም አስገኝ የሁሉ ፈጣሪ መኾኑ የታወቀ ነው። በተለይ ግን በውኃ ላይ አድሮ የመታየቱ ነገር ምሥጢር አዘል ሆኖ ይገኛል። በብዙ መልኩ መንፈስ ቅዱስ በውኃ እያደረ አድኖዋል። ለምሳሌ በዮርዳኖስ ወንዝ ንዕማን ከለምጹ ሊነጻ የቻለው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋው በውኃው ላይ ስለነበር ነው። ውኃ ብቻውን ፀበል መኾን አይቻለውም። መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ውኃ የኾነ እንደኾነ ምክንያተ ፈውስ ይሆናል። (ዘፍ.፩፥፪፣ ፪ነገ.፭፥፰—፲፬) ዛሬም ቢኾን መንፈስ ቅዱስ በዘይት አድሮ እንደሚያድን በውኃ አድሮ ሲያድን ይታያል። ፀበል የምንለውም የተቀደሰ ውኃ መዳኛ የሚኾነው አዳኝ (ማሕየዊ) መንፈስ ቅዱስ ስላደረበት ነው። (ሚኔራል) ንጥረ ነገር ወይም ሌላ ቅመማ ቅመም ስላለበት አይደለም። (ሚኒራልም) ኖረበት አልኖረበት በመንፈስ ቅዱስ የከበረ ውኃ ለፈውስ ምክንያት መኾኑ አያጠያይቅም። ይኸንንም ለማወቅ በፀበል አማካይነት የሚፈጸመውን ፈውስ ደኅና አድርጎ በማጥናት መረዳት ይቻላል።

መድኃኒታችን በዮሐንስ ወንጌል የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ በውኃ መስሎ አስተምሮዋል። «ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ጌታችን ኢየሱስ ቆሞ ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ አሰምቶ ተናገረ። ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፣ ኢየሱስ ገና ስላል ከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና።» (ዮሐ.፯፥፴፯—፴፱)

ክርስቶስ በመስቀል ሞቶ ከተነሣ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ተሰጠ እንግዲህ መድኃኒታችን የተናገረው ቃል ፍጻሜውን አገኘ። በውኃ የተመሰለው መንፈስ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያንን ጥማት ለማርካት የሚነጻ የሚጠጣ፣ በመኾኑ ተሰጠ። ስለዚህ ነው መንፈስ ቅዱስ በውኃ ይመሰላል የተባለው። በቀሌምንጦስ መጽሐፍ ተጽፎ እንደሚገኘው መድኅን ክርስቶስ ውኃን ለአንድነት ለሦስትነት ምሳሌ አድርጎ ሲያስተምር «አቡየ ማይ ወእነ ጣዕሙ ወመንፈስ ቅዱስ ሕይወቱ» ብሏል «አባቴ በውኃው አካል እኔ ከውኃው ጣዕም መንፈስ ቅዱስ በውኃው ሕይወትነት ይመስላል» ማለት ነው።

ውኃ ሦስትነት አለው አካሉ ጣዕሙ ሕይወትነቱ ነው። በአካሉ አብ በጣዕሙ ወልድ በሕይወትነቱ መንፈስ ቅዱስ ይመሰላሉ። በሕይወት ለሚንቀሳቀስ ፍጥረት ለሰው ለእንስሳትና ለዕፅዋት ሁሉ ውኃ ሕይወታቸው ነው። ውኃ ካጡ በጥም ይሞታሉ በድርቅ ይጠወልጋሉ ከልምላሜ ከጽጌ (አበባ) ከፍሬ ይለያሉ። ከሥራቸው ጀምሮ ግንዳቸው አገዳቸው ቅጠላቸው ይደርቃል። አበባቸው ፍሬያቸው ይረግፋል ልምላሜያቸውን ያጣሉ ይጠወልጋሉ ይደርቃሉ ይኸ ሁሉ ችግር ውኃ በማጣት የሚከሰት ጣጣ ነው። በዚሁ አንጻር ሰውም በውኃ የተመሰለው መንፈስ ቅዱስ ካላደረበት ከመንፈስ ቅዱስ ውኃነት ከተለየ በነፍሱ ይጠማል ደስታን እርካታን አያገኝም ሰላም ሕይወት አይኖረውም ልምላሜ ነፍስ ያጣል ከትሩፋት አበባ ከጽጌ ምግባር ከፍሬ ጸጋ የተለየ መንፈሳዊ ሕይወቱ የጠወለገ የወየበ ይሆናል። በሃይማኖቱም ሥር የለሽ መሠረተቢስ ይሆናል መንፈሳዊ ሕይወቱ አደጋ ላይ ይወድቃል።



www.ethiopisnorthodox.org

ስለዚህ ልምላሜ ነፍስን የሚሰጠው ልቡን በሃይማኖት የሚያጸናለት መንፈሳዊ ዕድገት እንዲኖረው የሚያደርግለት የትሩፋት አበባ እንዲያብብ የክብር ፍሬ እንዲያፈራ የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው። ልበ አምላክ ዳዊት ስነፍጥረትን ምሳሌ በማድረግ ሲናገር «ዘአጽንዓ ለምድር ዲበ ማይ» ይላል (መዝ.፻፴፭፥፮) በዘይቤው ሲፈታ ጥቅሱ «ምድርን በውኃ ላይ አጽንቶ የፈጠረ እሱ ነው» ተብሎ ይነበባል። ምድር በውኃ ባትጸና ውስጥ ለውስጥም ውኃን ባትጠጣ እንደ ጎታ (እንደጎተራ) ሁሉ በፈረሰች ነበር። ይኸን ለመረዳት በድርቅ ወራት ውኃ በማጣታቸው ተራሮች ኮረብቶች ገደላ ገደሎች ሲፈርሱ ሲናዱ ይታያሉ። ሌላውም ምድር ነፋስ ሲበትነው ሲዘራው ይታያል። ውኃ መሬትን እንዳትፈርስ እንደሚያጸናት መንፈስ ቅዱስም በመሬት የተመሰለውን ሰው በኃጢአትና በክህደት እንዳይፈርስ በሃይማኖትና በምግባር እንዲጸና ያደርገዋል። ጻድቃን ዱር ለብሰው ጤዛ ልሰው ደንጊያ ተንተርሰው በተባሕትዎ በምናኔ ከሰው ተለይተው ከበዓት ተከተው ጾብአ አጋንንቱን ድምፀ አራዊቱን ግርማ ሌሊቱን ሐሩረ ፀሐዩን ረሀቡን ጽሙን ታግሰው ችለው የሚኖሩት በገድል በትሩፋት የሚጸኑት መንፈስ ቅዱስ እያጸናቸው ነው።

ሰማዕታትም ስለቱን እሳቱን መስቀሉን ስደቱን ፀዋትወ መከራውን የሚታገሡት በጥብዓት (ጨክነው በሰማዕትነት) የሚሠዉት የሚወገሩት የሚሰየፉት መንፈስ ቅዱስ ስለሚያጸናቸው ነው። ሕዝባውያን በሕግ በተክሊል በሥርዓት በቁርባን መነኮሳት ደናግል በንጽሕና በድንግልና የሚፀኑት መንፈስ ቅዱስ ኃይሉን ስላሳደረባቸው ነው። እንግዲህ መንፈስ ቅዱስን በውኃ ሰውን በምድር መስሎ ክቡር ዳዊት ትንቢት እንደተናገረ እናስተውል። የቤተክርስቲያን ምሁራን ምድር ሰውን እንዴት እንደምትመስል ሲያመሳጥሩ «ምድር ሰውን ትመስላለች ሰውም ከምድር ጋር ይመሳሰላል። በምድር ውስጥ ውኃ እንዳለ በሰው ውስጥም ደም ውኃ አለ ምድር በደንጊያ በእንጨት ጸንታ ትኖራለች ሰውም በአጥንት በሥር (በጅማት) ጸንቶ ይኖራል። የምድር መሬትነቷ እንደ ሰው ሥጋ ነው በላይዋ ላይ ያለው ሣርም እንደ ሰው ፀጉር ነው። በሰው ፀጉር ይመሰላል» ይላሉ ሰው በምድር መመሰሉ በሊቃውንት ቃል ብቻ የታተተ የተገለጸ አይደለም። ራሱ ክቡር ዳዊትም በመዝሙሩ ገልጾታል። «ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ» ይላል (መዝ.፺፰፥፩) ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ ማለቱ እንደሆን ግልጽ ነው።

ውኃ ምድርን እንደሚያጸናት በውኃ የተመሰለው መንፈስ ቅዱስም ሰውን በሃይማኖት በምግባር የሚያጸናው መኾኑን ተገንዝበን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመጠበቅ ቅዱሳንን እንምሰላቸው እንከተላቸው።

ውኃ ለፈለገ ሁሉ ለድሀውም ለባለጠጋውም ይገኛል የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በሃይማኖት ለፈለገ በጸሎት ደጅ ለጠና ሁሉ ያለ ልዩነት ሊሰጥ ይኖራል ስለዚህ እኛም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋው እንዳይለየን በዝቶ እንዲሰጠን ፈጣሪያችንን ሁል ጊዜ ሌትም ቀንም በጸሎት በጦም ደጅ ልንጠናው ይገባናል። (ሉቃ.፲፩፥፲፫፤ ምዕ.፲፰፥፯)

ውኃ አጥናፍ እስከ አጥናፍ ይፈሳል መንፈስ ቅዱስም በሁሉ ቦታ ይገኛል በመላእክት በጻድቃን በቅዱሳን በነቢያትና በሐዋርያት በምዕመናን ላይ ሁሉ አድሮ ይኖራል።

ውኃ ያነፃል መንፈስ ቅዱስም መንጽሒ ነው ሰውን ከኃጢአት ያነጻል፤ በውኃ የታጠበ ልብስ በቶሎ አያረጅም ለብዙ ጊዜ በአዲስነቱ ይቆያል። መንፈስ ቅዱስም ያደረበት ሰውነትም በሥጋ በነፍስ በልቡና ንጹሕ ይሆናል። መንፈሳዊ ኃይል ጽናት ይኖረዋል በኃጢአት አያረጅም ሁል ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ አዲስ ሕይወት አግኝቶ ከብልየት ታድሶ ይኖራል።

ቤት በእሳት ቢቃጠል መጥፋት የሚቻለው በውኃ ነው የሥላሴ ማደሪያ የሆነ የክርስቲያን ሰውነትም በኃጢአት በፍዳ በኩነኔ እንዳይቃጠል ከዚህ የሚያድነው በውኃ የተመሰለው መንፈስ ቅዱስ ነው። የኃጢአት እሳትነትን ፍዳውን ያጠፋለታልና።

በእርሻ የተዘራው መልካም ዘር አንዱ ቅንጣት ሠላሳ ስድሳ መቶ ፍሬ ሊሰጥ የሚችለው በመሬቱ ለምነት ብቻ አይደለም ከላይ በሚወርድለት የዝናም ውኃም ነው እንጅ (ማቴ.፲፫፥፳፫፤ ፩ቆር.፫፥፱)

የእግዚአብሔር እርሻ በተባሉት ክርስቲያኖች ልብ ውስጥ የተዘራው መልካም ዘር ቃለ ወንጌል በቅሉ ምዕመናንን ለንጽሐ ሥጋ ለንጽሐ ነፍስ፤ ለንጽሐ ልቡና ሊያበቃቸው የሚቻለው በጥምቀት ጊዜ በሚርን በተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ሀብተወልድና (የልጅነት ስጦታ) መሠረት ነው።

መንፈስ ቅዱስ ውኃ ዘርን እንደሚያበዛው የወንጌልን ቃል በጠቅላላው የቅዱሳት መጻሕፍትን ንባባቸውን አንዱን ገጽ ንባብ በትርጓሜ በምሥጢር በገድል በተአምራት እንዲበዛ በማድረግ ምሥጢራት ሀብታትን ሲያድል ይኖራል። ስለዚህ ከውኃ የተለየ ዘርና ተክል ደርቆ እንደሚቀር እኛ ክርስቲያኖች በኃጢአታችን ልቡናችንን በማጽናት በጥርጥርና በክህደት እልከኝነት ጸር እንዳንገኝ ሁል ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ውኃነት ልንለመልም ልናፈራ ይገባናል። በጎ ፍሬ ማፍራት የሚቻለንም እንደ ተጠማች ምድር ከላይ የሚወርድልንን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ጠጥተን ስንገኝ ነው። የቅዱሳንን ሰውነት ያለመለመና ከፍሬ ክብር ያደረሰ መንፈስ ቅዱስ በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኘነውን ሁሉ በሃይማኖተ ወንጌል ያለምልመን በምግባረ ወንጌል ከፍሬ ክብር ከጸጋ ያድርሰን አሜን። ✝

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።



www.ethiopisnorthodox.org